ዳግም የተወለደ አጋንንትን በክርስቶስ ኢየሱስ ስም ያወጣል እንጂ አጋንንት አይገቡበትም። ስለዚህ እኛ ክርስቲያኖች በቅድስና፣ በፍቅርና በትህትና እየኖርን ከእምነት ወደ እምነት፣ ከኃይል ወደ ኃይል፣ ከክብር ወደ ክብር በእግዚአብሔር ቃልና በእግዚአብሔር መንፈስ እያደግን - ክርስቶስን እየመሰልን በክርስቶስ ኢየሱስ ስም፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና በቃሉ ሥልጣን በዲያብሎስ የተያዙትን ነጻ እንድናወጣ ተጠርተናል።

ዳግም በተወለድን አጋንንት ባይገቡብንም ጠላት ዲያብሎስ የሚንበለበሉ ፍላጻዎች በመወርወር በውጪ ሊያጠቃን ስለሚዋጋን የእግዚአብሔር ዕቃ ጦር ሁሉ ማንሳትና መልበስ አለብን። ዳግም ተወልጃለሁና ምንም አይደለም በማለት ኃጢአትን እንለማመድም፣ የዲያብሎስን ሽንገላ ቸል አንልም።

ልብ ማለት ያለብን ነገር ደግሞ የሥጋ ድካምና በሽታ ሁሉ ከመናፍስት እንደሆነ አድርገን መውሰድ የለብንም። እግዚአብሔርን ካለመታዘዝ፣ በኃጢአት፣ አንድ ሰው በቂ እንቅልፍ ካልተኛ ወይም ካላገኘ፣ ምግብ ካልበላ፣ ሰውነቱን እንደሚገባ ካልተንከባከበ ድካምና በሽታ ሊመጡ ይችላሉና።

ሰይጣን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዳይኖርህ፣ መከናወን እንዳታገኝ፣ በቃሉ እንዳትጸና፣ በመንፈስ ቅዱስ እንዳትሞላ፣ ከጌታ ፈውስን እንዳትቀበል፣ ጌታን እንዳታገለግል በተለያየ አይነት መንገድ ይዋጋሃል። አይዞህ አንተም ለጢሞቴዎስ እንደተነገረው በ1ጢሞ. 1:18 መልካሙን ጦርነት ተዋጋ ተብሎ በቃሉ ተጽፏልና መልካሙን ጦርነት ተዋጋ። በእርሱ በወደደን ከአሸናፊዎች ሁሉ ትበልጣለህ።

በዚህ መጽሐፍ ክርስቲያን ማለትም ዳግም የተወለደ በክፉ መናፍስት ላይ ሥልጣን እንደተሰጠውና በዲያብሎስ የተያዙትንና የታሰሩትን በክርስቶስ ኢየሱስ ስም ነጻ ማውጣት ስለሚቻልበት በሰፊው ተዘርዝሯል እንደዚሁም ደግሞ ሰዎች በአጋንንት እንዳይገዙ ታላቅ ማስጠንቀቂያን ይዟል።

ይህን መጽሐፍ በምታነቡበት ጊዜ በእግዚአብሔር ቃል እምነት እንዲኖራችሁ፣ የመንፈስ ቅዱስ እሳት ልባችሁን እንዲሞላውና አጋንንትን የምታወጣው የእግዚአብሔር ጣት ዘወትር ከእናንተ ጋር እንድትሆን ጸሎቴነው።

*ገብሩ ወልዱ*
*ጥቅምት 1990*
*አዲስ አበባ*



# *ምዕራፍ አንድ*
# *ዲያብሎስና መላእክቱ*

እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ከፈጠረ በኋላ አገልጋዮቹ እንዲሆኑ አዕላፋት የሆኑ መላእክትን ፈጠረ። በተለይም ደግሞ አንዱን መልአክ በውበት፣ በችሎታና በጥበብ ውብ አድርጎ ፈጠረው፤ ቀባውም። የመልአኩም ስም - የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ይባል ነበረ። እግዚአብሔር በሰጠውም ሥልጣን የእግዚአብሔርን ክብር ይጋርድ ነበር። ነገር ግን ከእግዚአብሔር በተቀበለው ነገር በመታበዩና ስግደትና አምልኮን እንዲደረግለት በመፈለጉ ከሰማይ ተጥሎ ከፍጥረት ሁሉ በታች በመሆን የኃጢአት፣ የክፋት፣ የመከራና የፈተና ምንጭ ሆነ። ስሙም ሰይጣን ማለት - ጠላት፣ ባለጋራ ተባለ።

> *"አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ እንዴት እስከምድር ድረስ ተቆረጥህ! አንተም በልብህ ወደ ሰማይ አርጋለሁ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ በሰሜን ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ ከደመናዎች ከፍታ በላይ አርጋለሁ በልዑልም እመስላለሁ አልህ። ነገር ግን ወደ ሲኦል ወደ ጉድጓድ ጥልቅ ትወርዳለህ" (ኢሳ. 14:12-14፤ ሕዝ. 28:12-17)*

እግዚአብሔርም ሰይጣንና መላእክቱን ከሰማይ ወደ ምድርና ወደ ሲኦል ጣላቸው። ሰይጣን በአየር፣ በምድር ላይ እና በባህር በሚኖሩት ሁሉ ላይ ሥልጣን የነበረውን አዳምን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲተላለፍ በማድረግ የበላይነትን ተቀዳጀ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰይጣንና አጋንንቱ አየሩን፣ ምድሩንና ባህሩን ሞሉት። ስለዚህ ሰይጣን የአየር አለቃ መንፈስ፣ የዚህ ዓለም ገዢ፣ አብዶን ማለት - የጥልቁ ገዢ ተባለ። (ሉቃ. 10:18፤ 2ጴጥ. 2:4፤ ይሁዳ 6፤ ራዕይ 12:9፤ ዮሐ. 12:31፤ ኤፌ. 2:2፤ ራዕይ 9:11)

## 1.1 ሰይጣን ማን ነው?

ሰይጣን የክፋትና የኃጢአት ሁሉ ምንጭ የእግዚአብሔርና የሰው ዘር ጠላት የሆነ ፍጡር ነው። ኃይል አለው ነገር ግን ሁሉን ቻይ አይደለም፣ እውቀት አለው ነገር ግን ሁሉን አዋቂ አይደለም፣ በዓለም ሁሉ ይሠራል ነገር

ግን በአንድ ጊዜ በሁሉ ሥፍራ መገኘት የሚችል አይደለም። ትልቁ ሥራውም መስረቅ፣ ማረድና ማጥፋት ነው። (ዮሐ. 10:10)

## 1.2 ሰይጣን መኖሪያው የት ነው?

ሰይጣን ክፉ ሥራውን የሚሠራው በጥልቅ፣ በምድር፣ ወይም በአየር ነው። በአንድ ጊዜ በሁሉም ቦታ መገኘት ስለማይችል ዙፋኑን በአንድ ቦታ አስቀጦ በየአገሩ፣ በየከተማው፣ በየመንደሩና በየቤቱ የሚልካቸው አጋንንት አሉት። በሐዋርያት ዘመን ዙፋኑን ጴርጋሞን በምትባል ከተማ አድርጎ ነበር። ጴርጋሞን በአሁኑ ቱርክ በሚባለው አገር የነበረች ከተማ ናት። (ራዕይ 2:12-13)

## 1.3 ሰይጣን ምን ይመስላል?

ሰይጣን ውስን አውቀት፣ ጥበብና ኃይል ያለው በሥጋ ዓይን የማይታይ መንፈስ የሆነ ፍጡር ነው። ሰይጣን ለዓላማው ሲል ራሱን የሚለዋውጥ ይህም ሰውን በተለይም ክርስቲያኑን ለማሳት በብርሃን መልአክ የሚመስል፣ የዓለምን ሕዝብ ለመግዛት በብርቱ ዘንዶ የሚመስል፣ ለማሳት ሲፈልግ እንደ እባብ ተንኮለኛ፣ ለመዋጥ ሲፈልግ ደግሞ እንደ አንበሳ የሚያገሳ በአጠቃላይ ለዓላማው ሲል አቀራረቡን የሚለዋውጥ ፍጥረት ነው።

ሰይጣን ማበላሸት፣ ማጥፋት፣ ማረድና መግደል እንጂ መፈወስ፣ መፍጠር፣ መትከል፣ መገንባት፣ ማበጀትና መጠበቅ ባህሪው ያልሆነ ሐሰተኛና የሐሰት ሁሉ አባት ነው።

## 1.4 የሰይጣን ሰብዕና (Personality of satan)

በኢዮብ 1:8-11፣ 2:3-5፣ ማቴ. 4:3-11 መሰረት ሰይጣን ክፉ፣ ጨካኝ፣ ምህረት የሌለውና የማያውቅ፣ ስግብግብ፣ መራርነት የተሞላ፣ ሐሰተኛ፣ ሌባ፣ ሰላም የሌለው፣ የታወከ፣ አጥፊ፣ ስጉ፣ ድንጉጥና ፈሪ፣ መልካምነት የሌለበት፣ ርኩስ፣ ተንኮለኛ፣ ጠማማ፣ ተቃዋሚና ትዕቢተኛ ነው።(ኢሳ. 14:12-14፣ 1 ዮሐ. 2:13፣ 2 ቆሮ. 11:3፣ 1 ነገስ. 22:21፣ ማቴ. 12:29)



## 1.5 ሰይጣን የሚጠራባቸው ስሞች

ከመውደቁ በፊት የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ (ሉሲፈር) ተብሎ ይጠራ ነበር (ኢሳ. 14:12) በሕዝ. 28:14 መሠረት ደግሞ የተቀባ ኪሩብ ይባል ነበር። ከወደቀ በኋላ የተለያየ ስም አለው ስሙም ርኩስና ክፉ ከሆነው ሥራው ጋር የተያያዘ ነው።

ሰይጣን ------------------ ባላጋራ፣ጠላት፣ (ማቴ.4:10፣3:1)
ዲያብሎስ - ----------------- ከሳሽ (ማቴ. 4:1፣ ዮሐ. 8:44)
እባብ - -------------------- (ዘፍጥ. 3:1፣ ራዕ. 12:9)
ዘንዶ - -------------------- (ራዕ. 12:3-17)
አብዶን አፖሎን - -------አጥፊ (ራዕ. 9:11)
ቤልሆር - ------------------ ዋጋ የሌለው ክብር ያጣ (2ቆሮ. 6:15)
ብኤልዜቡል - ------------ የዝንቦች አለቃ (ማቴ. 12:24-27)
ጠላት - --------------------- (ማቴ. 13:39)
ባላጋራ - ------------------- (1ጴጥ. 5:8)
ጨቋኝ ገዢ - --------------- (ሐዋ. 10:38)
ከሳሽ - ---------------------- (ራዕ. 12:10)
ነፍስ ገዳይ - --------------- (ዮሐ. 8:44)
ሐሰተኛ - ------------------- (ዮሐ. 8:44)
የአየር አለቃ መንፈስ - --(ኤፌ. 2:2)
የዚህ ዓለም አምላክ - ----(ዮሐ. 12:31፣ 14:30፣ 16:11)
ፈታኝ - --------------------- (ማቴ. 4:3)
ሌባ - ----------------------- (ዮሐ. 10:10)
የክርስቶስ ተቃዋሚ - ----(1ዮሐ. 4:1-4)
የጥልቅ መልአክ - --------(ራዕ. 9:11)
ክፉ - ------------------------ (ማቴ. 13:19)
ወጥመድ - ----------------- (መዝ. 91:3)

# ምዕራፍ ሁለት
# የአጋንንት ማንነት

ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ባመጸ ጊዜ ከእርሱ ጋራ ያበሩ መላእክት - የተጣሉ መላእክት አጋንንት፣ ክፉ መናፍስትና ርኩስ መናፍስት ሆኑ። ስለዚህም ሰይጣን የአጋንንት አለቃ ይባላል። ማቴ. 24:48፣ 12:24

## 1. ሀልውናቸው

- መናፍስት ናቸው ማለትም ሥጋና ደም የላቸውም። (ራዕ. 16:13)
- ሰብዕና (Personality) ያላቸው ፍጡራን ናቸው ይህም እውቀት፣ ስሜትና ፈቃድ አላቸው። (ሉቃ. 4:33-35፣ ሐዋ. 16:16-17፣ ያዕ. 2:19)

## 2. ችሎታቸው

ከሰው የበለጠ እውቀት፣ ኃይልና ብርታት አላቸው። ይህን ደግሞ ክፉ ለሆነው ሥራቸው ይጠቀሙበታል።(ሉቃ.8:29፣ሐዋ.16:16-17፣2ተሰሎ.2:9፣2 ጴጥ.2:11)

- የሰው ስቃይ ምንጭ ናቸው። (ማቴ. 4:2-4፣ ሐዋ. 5:1-5፣ 8:22፣ ዕብ. 2:14)
- መናፍስት ስለሆኑ ተፈጥሮዊ አጥር (ግድግዳ አያግዳቸውም (ሉቃ. 8:30፣33፣11:24-26)
- በሽታን ያመጣሉ (ሉቃ. 7:21) በሽታ ሁሉ ከአጋንንት ባይሆንም የሚያመጡት በሽታ ግን አለ።
- ተፈጥሮን ያዛባሉ (ኢዮ. 1:18-19፣ ማር. 4:37፣39)

## 3. ተፈጥሮአቸው

- የመልካም ሁሉ ጠላት ስለሆኑ ክፉና እርኩሳን መናፍስት ተብለው ይጠራሉ። (ሉቃ. 8:30፣33፣ 11:24-26) በክፋትም አንዳቸው ከአንዳቸው ይበልጣሉ። (ማቴ.12:45)
- አሳቾች ናቸው (2ቆሮ.11:3፣1ጢሞ. 4:1፣ ራእ. 12:9፣ ገላ. 1:8) የሚያስቱትም ዓለሙን በሙሉ ሲሆን ክርስቲያኖችን እንኳ ሳይቀር ለማሳት ይሞክራሉ። ይህ በሔዋን ስለሰራላቸው አሁንም ለማሳት ብዙ ትምህርት ያሠራጫሉ።

> *"ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመ እባብ ተጣለ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።" (ራእ. 12:9)*

## 4. አደረጃጀታቸው



## 4. አደረጃጀታቸው

በኃይልና በሥልጣን ተዋረድ የተደራጁ ናቸው። ይህም በውትድርና ሳይንስ እንዳለው አይነት አደረጃጀት ሲሆን ደረጃውም በኤፌ. 6:12 መሠረት አለቆች፣ ሥልጣናት፣ የዚህ ጨለማ ዓለም ገዢ መናፍስት፣ በአየር ላይ ያሉ ክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት፣ የአየር አለቃ መንፈስ ሲሆን በቆላስ. 2:10፣15 መሠረት ደግሞ አለቆችና ሥልጣናት ይባላሉ። አንዳንድ መናፍስት በቦታዎችና በአገሮች ላይ ሥልጣን አላቸው። የሚገዙአቸውን ቦታዎች ላለመልቀቅ ይፈልጋሉ። ለምሳሌ:-

- . በማር. 5:1-20 ያለው የሌግዮን መንፈስ የሆነው የርኩስ መንፈስ (ልብስን የማያስለብስ ኀፍረተ ሥጋን የሚገልጥ) ጌታ ኢየሱስም "ውጣ!" ባለው ጊዜ ከዚያ እንዳያስወጣቸው አጥብቀው ለመነው ይህም የዚያን አከባቢ ሰዎች እስራኤላውያን እንዲያረቡ ያልተፈቀደላቸውን እሪያ ያረቡ ስለነበር ነው። ለዚህ ነው ክሰዎች አጋንንት ስናወጣ ወደ አገሬ፣ ወደ ቀዬ ስደዱኝ ብሎ የሚናገረው።
- . በሕዝ. 28 እንደምንመለከተው ጢሮስ ለምትባለው አገር ገዢዋና ንጉሥዋ የነበረው ሰው ብቻ ሳይሆን ሰይጣንም እንደነበር ይናገራል።
- . በዳን. 10:5-13 ዳንኤል ሲጸልይ የፋርስ አለቃ መንፈስ (በፋርስ መልክዓ ምድር የሚገኙት አጋንንት አለቃ) ከእግዚአብሔር ዘንድ ለዳንኤል መልስ ይዞ የመጣውን መልአክ 21 ቀን በአየር ላይ ተቋቋመው ስለዚህም የመላእክት አለቃ የሆነው ሚካኤል የፋርስ አለቃ መንፈስን ተዋጋ። ሚካኤል ሰይጣንን ሲገስጽ በራሱ ሥልጣን ሳይሆን በእግዚአብሔር ሥልጣን ነው የሚገስጸው (ይሁዳ 9)

## 5. ውስንነታቸው:-

- ሰይጣንና አጋንንት ፍጡራን እንደመሆናቸው መጠን በሁሉ ነገር የተወሰኑ ናቸው። ይህም:-

### ሀ. በኃይልና በሥልጣን ውስን ናቸው።

እግዚአብሔር በኢዮብ ሕይወትና ንብረት ላይ ቅጥር ስላደረገ ሰይጣን ምንም እንኳን በምድር ፊት ቢመላለስም ኢዮብንና ንብረቱን ሊጎዳ አልቻለም።

(ኢዮብ 1:10) ሰይጣን በጠየቀው መሠረት እግዚአብሔር ፈቅዶለት በመጀመሪያ የኢዮብን ንብረት ማለትም የኢዮብን አህዮች፣ በሬዎች፣ በጎች፣ ግመሎች፣ ባርያዎች ልጆቹን በኋላም የኢዮብን ሥጋ ሊጎዳ ቻለ። (ኢዮብ 1:11-19፣ 2:1-8፣ ማቴ. 10:28)

### ለ. በጊዜ የተወሰኑ ናቸው

*መጀመሪያ አላቸው "ኢየሱስ ሆይ፥ የእግዚአብሔር ልጅ፥ ካንተ ጋር ምን አለን? ጊዜው ሳይደርስ ልታሰቃየን ወደዚህ መጣህን? እያሉ ጮኹ።"* **(ማቴ. 8:29)**

> *"ስለዚህ ሰማይና በውስጡ የምታድሩ ሆይ ደስ ይበላችሁ ለምድርና ለባህር ወዮላቸው ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ ወደ እናንተ ወርዷልና።"* (ራዕ. 12:12)

አጋንንት ክፉና እርኩስ ሥራቸውን የማይሠሩት ለዘለዓለም ወደ እሳት ባህር በሚጣሉበት ጊዜ ነው። ሰይጣን ይህ ጊዜ አጭር መሆኑን አውቆ በታላቅ ቁጣ የማረድ፣ የመግደልና የማጥፋት ተልዕኮውን ለማከናወን ይጥራል።

እነዚህ አጭር ጊዜዎች ክፉ ቀኖች ናቸው። በኤፌ. 5 *"ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ"* ይላል። ስለዚህ ቀኖቹን ጠላት እንዳይጠቀምባቸው ልንዋጃቸው ይገባል። የምንዋጀውም የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ ነው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናውቀው ደግሞ በእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ቅዱስን በመሞላት ነው። አጋንንትን ማውጣት ማለት ጊዜአቸው ሳይደርስ ማሰቃየት ማለት ነው።

### ሐ. በስፍራ የተወሰኑ ናቸው።

ሰይጣን በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ መገኘት ባይችልም በየሥፍራው ሁሉ ለክፉ ሥራው አጋንንቱን ይልካል። (ራእ. 2:13) የሚሠሩበት ሥፍራም በመንፈሳዊ ጨለማ ሥፍራ ሲሆን ወደ ብርሃን አይመጡም። (ዮሐ. 3:20) ስለዚህ በብርሃን ስንመላለስ ሰይጣን ሊያጠቃን አይችልም ማለት ነው። (ቆላ. 1:13)

በዚህ ዘመን ሰይጣን እና አጋንንት በኃይል እንዳይሠሩ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ታግደዋል።

> *"የዓመጽ ሚስጢር አሁን ይሰራልና ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ።"(2 ተሰሎ. 2:7)*



> *"እኔም እልሃለሁ አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።"* (ማቴ. **16:18)**

ክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀል ላይ የዲያብሎስን ራስ ቀጥቅጦ በትንሳኤው አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ የቤተክርስቲያን ራስ በመሆን ሥልጣንን አካሉ ለሆነችው ለቤተክርስቲያን ሰጥቷል።

> *"እነሆ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ"* (ሉቃ. 10:19)

የሰይጣን ዋና ሥፍራው በሰማያዊ ሥፍራ ነው። ሰይጣን በኤፌ. 2:2 *"በአየር ላይ ሥልጣን ያለው አለቃ"* ተብሎ ሲጠራ በ2ቆሮ. 4:4 *"የዚህ ዓለም አምላክ"* ተብሏል። በዮሐ. 14:30 ደግሞ *"የዚህ ዓለም ገዢ"* ተብሏል።

ሰይጣንና መላእክቱ በሰማያዊ ሥፍራ ያሉ ሠራዊት ቢሆኑም የእነርሱን ራስ የቀጠቀጠና አለቅነታቸውን የገፈፈ የናዝሬቱ ኢየሱስ ከሁሉም በላይ ነው። *"እርሱ በሰማያት ያለፈ" (ዕብ. 4:14)* ታላቅ ሊቀካህናችን ነው። ኢየሱስ የሰይጣንን ግዛት በድል አድራጊነት ጥሶ ያለፈ ደግሞም *"ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣ"* ጌታ ነው። (ኤፌ. 4:10)

## 2.1 የአጋንንት ብዛት

መጽሐፍ ቅዱስ የቅዱሳን መላእክት ብዛት ከቁጥር በላይ እንደሆነ ይናገራል። (ራዕ. 5:11 ዕብ. 12:22-23) የወደቁት መላእክት ቁጥርም ብዙ ነው። ምክንያቱም አጋንንት የመላእክት ሲሶ ናቸውና። (ራዕይ 12:4)

በራዕ.9:1-11 ስንመለከት የጥልቁ ጉድጓድ ተከፍቶ ፀሐይንና አየርን የሚያጨልም ጢስ ወጣ። ከጢሱም ውስጥ አብዶን ወይም አጶልዮን የሚባል ንጉሥ ያላቸው የሚያሰቃዩ መናፍስት ወጡ። እነዚህ መናፍስት አጋንንት እንደሆኑ ግልጽ ሲሆን ቁጥራቸውም እጅግ ብዙ ነው። በራዕ.9:13-16 በታላቁ በኤፍራጥስ ወንዝ አራቱ መላእክት በተፈቱ ጊዜ የዓለምን ሕዝቦች ሲሶ የሚገድል እሳትና ጢስ ዲንም ከአፋቸው የሚያወጡ ሠራዊት ወደ ምድር ሁሉ እንደሚወጡ እናያለን ብዛታቸው እልፍ ጊዜ እልፍ ነው።

በሰው ውስጥ እጅግ ብዙ አጋንንት ሊያድሩ ይችላሉ። በማር. 5 ጌርጌሴኖን በሚባል አካባቢ ይኖር በነበረው ሰው ውስጥ ያደረ አጋንንት ጌታ ኢየሱስ አጋንንቱን ስሙን በጠየቀው ጊዜ ሌጌዎን ነን አለ። ሌጌዎን ማለት

ጭፍራ ማለት ሲሆን በሮም የወታደር አደረጃጀት 3000 - 6000 ሠራዊት ያለው ማለት ነው። ይህ ሰው 3000 - 6000 አጋንንት አድረውበት ነበር ማለት ነው። መግደላዊት ማርያም ውስጥ የነበሩ አጋንንት ደግሞ ሰባት ነበሩ። በማቴ. 12:43-45 ርኩስ መንፈስ ከሰው በወጣ ጊዜ ወደ ነበረበት ሲመለስ ባዶና (ተጠርጎ ለእርሱ የተመቸ ሆኖ) አጊጦ (እርሱን የሚቀበል፣ የሚያስተናግድ) ሆኖ ባገኘው ጊዜ ወዲያውኑ ሳይስጥ ከዚያ ሄዶ ሌሎች ሰባት አጋንንት ጨምሮ እርሱ ስምንተኛ ሆኖ ወደዚያ ቤት እንደሚገቡ ይናገራል።

ስለዚህ አጋንንት ብዙዎች ስለሆኑ በምናወጣበት ጊዜ ቁጥራቸውንም ጭምር ተናግረው እንዲወጡ ማዘዝ ተገቢ ነው።

## 2.2 በአገራችን በተለያየ ሥፍራ በብዛት የሚታወቁ መናፍስት

አጋንንት በተለያየ የዓለም ክፍል ከሀገሩ ባህል ጋር ተመሳስለው በሰዎች ውስጥ በማደር ክፉ ሥራቸውን ያስተላልፋሉ። ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ የፋርስ መንግሥት አለቃ የሚባል መንፈስ ነበር እንዲሁም የግሪክ አለቃ የሚባል መንፈስም ነበር። መናፍስት ባህልን ከለላ የሚያደርጉበት ምክንያት ባህል የዚህ ዓለም መዋቅር (World system) ክፍል በመሆኑና ሰዎች የኛ፣ ከአያቶቻችን፣ ከቤተሰቦቻችን፣ ከወላጆቻችን የተቀበልነው ነው ብለው ስለሚይዙት ነው። እንዳንዱ ባህል ከባዕድ አምልኮ ጋር ፈጽሞ የተያያዘ በመሆኑ ሰዎችን ይጎዳል። ለአጋንንትም ጥሩ መሣሪያቸው ነው። በሃገራችን በብዛት የሚታወቁ መናፍስት የአድባር መንፈስ፣ የመተት መንፈስ፣ አለማት፣ ድግምት፣ ዛር፣ ውቃቢና ጥንቆላ ናቸው።



# ምዕራፍ ሦስት
# የክፉ መናፍስት ስሞች

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በማቴ. 12:29 እና፣ ሉቃ. 11:21-22 ስለ ኃይለኛ ሰው ይናገራል። ይህ ኃይለኛ የተባለው መንፈስ ያለውንና የያዘውን ነገር የሚጠብቀው ጋሻና ጦር ይዞ ነው። ይህም ጋሻ ራሱን የሚመከትበት ሲሆን ጦሩ ደግሞ በርቀት ያለውን የሚያጠቃበት የረጅም ርቀት መሣሪያው ነው።

*"ከእርሱ ይልቅ የሚበረታ መጥቶ ሲያሸንፈው ግን ታምናበት የነበረው ጋሻና ጦር ይወስድበታል"* ማለትም መሣሪያ እንደሌለው ወታደር ይሆናል። ስለዚህም ምርኮውን ያካፍላል።

> *"ኃይለኛ ሰው ጋሻና ጦር ይዞ የራሱን ግቢ ቢጠብቅ ያለው ገንዘቡ በሰላም ይሆናል ከእርሱ ይልቅ የሚበረታ መጥቶ ሲያሸንፈው ግን ታምናበት የነበረውን ጋሻና ጦር ይወስድበታል ምርኮውንም ያካፍላል።" (ሉቃ. 11:21)*
>
> *"... አለቅነትና ሥልጣናትን ገፎ ድል በመንሳት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው።"* (ቆላ. 2:15)

ከላይ ባየናቸው ጥቅሶች መሠረት ይህ በኃይለኛ ሰው የተመሰለው ማነው? ስሙስ ማን ይባላል? ሥራውስ ምንድነው?

ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ካገኘን በክርስቶስ ኢየሱስ ስም በቃሉ ሥልጣንና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ኃይለኛውን ሰው በግዛቱ ያሰራቸው ገንዘቤ የሚላቸው ሰዎችን በወንጌል እውነተኛነትና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነጻነትን በማወጅ ባዶ እናስቀረዋለን። ክፉ የሆነውን ሥራውን እንዳይሠራ በኢየሱስ ስም እናስረዋለን። ከዚያም በማቴ. 18:18 ባለው መሠረት በእግዚአብሔር ኃይል የተጠቃውን ሰው ነጻ እንዲወጣ እንፈታለን። (መዝ. 149)

አንድ ጦር ተሸነፈ የሚባለው የውጊያው መሪ የሆነው ሲያዝ ሲሞት ወይም ጥሎ ሲሸሽ እንደሆነው ሁሉ በመጀመሪያ ማጥቃት ያለብን ኃይለኛውን ሰው ነው።

ይህ «ኃይለኛ ሰው» የተለያዩ ስሞች አሉት። ስሞቹ ደግሞ የተለያዩ ክፋና ርኩስ ሥራውን ያሳያሉ። መናፍስት የሥጋ ሥራ መደገፊያቸው፣ መጠለያቸውና መከለያቸው አድርገው ቢጠቀሙበትም የሥጋ ሥራ ከመናፍስት ሥራ ይለያል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያዩ አይነት መናፍስት ተጽፈዋል እነዚህ መናፍስት ኃይለኛው ሰው ናቸው። የእነዚህን መናፍስት ስምና ሥራ በዝርዝር ስንመለከት:-

## 1. የሟርተኝነት መንፈስ

*"...አምላክህ እግዚአብሔር ወደሚሰጥህ ምድር በገባህ ጊዜ እነዚያ አሕዛብ የሚያደርጉትን ርኩሰት ታደርግ ዘንድ አትማር። "(ዘዳ. 18:9)*

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ተምረው እንዳያደርጉት የሚናገረው የአሕዛብ ርኩሰት ምንድነው? ለዚህ መልሱን በዘዳ. 18:10-14 ያለው ነው። እነርሱም:-

* ልጆችን በእሳት ማሳለፍ

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች ልጆቻቸውን ሞሎክ ለሚባል የአሞናውያን አጋንንት ይሰው ነበር። በአሁኑ ዘመንም ስንመለከት አንዳንድ ሰዎች ለአጋንንት ስለት ያቀርባሉ። ይህ ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት አፀያፊ ነው።

* ሟርተኛነት

አጋንንትን በመጠየቅ ስለወደፊት ነገር መተንበይ፣ ትንግርት በአጠቃላይ ከአጋንንት በሚገኝ እውቀት ስለ ሁኔታዎች መናገር ነው።

* ሞራ ገላጭነት
* አስማተኛነት
* መተተኛነት

ሰዎች፣ እና የሰዎች ነገር ማለትም ትዳራቸው፣ ሥራቸው፣ ትምህርታቸው፣ ወይም ደግሞ ንብረታቸው በአጋንንት ኃይል እንዲመታ ማድረግ ማለት ነው። ለምሳሌ ድግምትና፣ አንደረቢ በዚህ ውስጥ ይካተታሉ።

* በድግምት መጠንቆል

በተለያየ አይነት መንገድ ጥንቆላን ማካሄድን ያጠቃልላል።



* ሙታንን መሳብ ናቸው።

1 ሳሙ. 28

የእግዚአብሔር ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ ሲመሩ ጠንቋዮች፣ ደብተራዎችና ሟርተኞች ደግሞ በሞርተኝነት መንፈስ ይመራሉ። የዚህ መንፈስ መሠረት መደገፊያው የሥጋ ሥራ ሲሆን (ገላ. 5:19-21) ክፉ ሥራውን የሚጠቀምባቸው መንገዶች ደግሞ:-

ሀ. አስማት (Magic) - (ዘዳ. 18:11፣ ዘጸ. 8:7፣ 9:11)

ለ. ከዋክብት ቆጣሪነት (አስትሮሎጂ)- (ኢሳ . 47:13፣ ዘሌዋ. 8:7፣ ኤር. 9:11)

ሐ. መተተኝነት - (ዘጸ. 22:18፣ ሚክ. 5:12)

መ. መናፍስት ጠሪነት - (ዘዳ. 18:11፣ ኢሳ. 19:3)

ሠ. አመፅ - (1ሳሙ. 15:23) እና የመሳሰሉ ናቸው።

እግዚአብሔር ስለ እነዚህ ነገሮች ምን ይላል?

*"የምትወርሳቸው እነዚህ አሕዛብ ሞራ ገላጮችንና ሟርተኞችን ያዳምጣሉ አንተ ግን <u>እንዲሁ ታደርግ ዘንድ አምላክህ እግዚአብሔር ከልክሎሃል</u>"* (ዘዳ. 18:14)

*"እናንተ ግን ... ነቢያቶቻችሁንና ሟርተኞቻችሁን ሀልም አላሚዎቻችሁንና ቃላተኞቻችሁን አትስሙ ከምድራችሁ እንዲያርቋችሁ እኔም እንዳሳድዳችሁ እናንተም እንድትጠፉ ሐሰተኛ ትንቢትን ይናገሩላችኋልና።" (ኤር. 27:9-10)*

ከዚህ እንደምንረዳው የሟርተኝነትን መንፈስ መከተል ሦስት መርገሞችን ያመጣል እነርሱም:-

* *እግዚአብሔር ከሰጠን ርስት መራቅን*
* *የእግዚአብሔር ፍቅር ፈንታ በቁጣው ሥር መሆን*
* *መጥፋት ናቸው።*

ስንት ሰዎች ይሆኑ በሟርተኝነት መንፈስ በሆነ ትንቢት ተመርተው እግዚአብሔር ካስቀመጣቸው ቦታ የተነቀሉ፣ የእግዚአብሔር ቁጣ በእነርሱ ላይ የነደደና ከእግዚአብሔርና ከእግዚአብሔር ቤት የጠፉ?

*"ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን በእሳት አሳለፉአቸው ሟርተኞችና አስማተኞችም ሆኑ፣ ያስቆጡትም ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ*

### 3. የቅንዓት መንፈስ -

*"ትሁት ልብ የሥጋ ሕይወት ነው ቅንዓት ግን አጥንትን ያነቅዛል።" (ምሳሌ 14:30)*

የቅንዓት መንፈስ ሰዎች በሌላው እንዲቀኑ የሚያደርግ ነው መደገፊያው የሥጋ ሥራዎች ሲሆኑ የመግለጫ መንገዶቹም:-

ሀ. ቅናት - (ምሳ. 14:30)

ለ. ፀብ - (ምሳ. 13:10)

ሐ. ጥላቻ - (ዘፍጥ. 37:4፣ 4:8)

መ. ብቀላ - (ምሳ. 6:34፣14:17)

ሠ. ነፍስ መግደል - (ዘፍጥ. 4:8)

ረ. ቁጣ - (ዘፍ. 4:5-6፣ ምሳ. 29:22-23)

ሰ. መለየት - (ምሳ. 10:12) የመሳሰሉት ናቸው

በዚህ መንፈስ ላለመጠቃት እርስ በርሳችን መዋደድ ይገባናል።

*"... እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትዕዛዝ እሰጣችኋለሁ። እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።" (ዮሐ. 13:34)*

### 4. ሐሰተኛ መንፈስ -

*"አሁንም እነሆ እግዚአብሔር በእነዚህ በነቢያትህ አፍ ሐሰተኛ መንፈስን አድርጓልና እግዚአብሔርም በአንተ ላይ ክፉ ተናግሮብሃል።" (2ዜና. 18:22)*

ሰይጣን ሐሰተኛና የሐሰት ሁሉ አባት ነው። (ዮሐ. 8:44) የዚህ መንፈስ መደገፊያው የሥጋ ሥራዎች ሲሆን የመግለጫ መንገዶቹም:-

ሀ. የኃይማኖት እስራት - (ገላ. 5:1)

ለ. ሐሰትን መናገር - (ምሳ. 6:16-19፣ 2ዜና.18:22)

ሐ. ክስ - (ራዕ. 12:8፣ መዝ. 31:18)

መ. ሐሜት - (1ጢሞ. 6:20፣ 2ጢሞ. 2:16)

ሠ. ያልሆኑትን መሆን - (ምሳ. 20:19 29:5)

ረ. የሐሰት ነብያት - (ኤር. 23:16-17 27:9-10 ማቴ.7:15)

ሰ. የሐሰት ሐዋርያት - (ራእ. 2:2)



ሸ. የሐሰት አስተማሪዎች - (2ጴጥ. 2:12)

ቀ. የሐሰት እረኞች እና የመሳሰሉት ናቸው።

### 5. ጠማማ መንፈስ

*"እግዚአብሔር የጠማምነትን መንፈስ በውስጥዋ ደባልቆአል ..."(ኢሳ. 19:14)*

ይህ ጠማማ መንፈስ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያጣምም፣ መልካሙን እንደ ክፉ የሚያሳይና ሰዎችን ወንድን ከወንድ ጋር፣ ሴትን ከሴት ጋር የሚያጋባ የሥጋን ሥራ መደገፊያው ያደረገ ሲሆን የመገለጫ መንገዶቹ:-

ሀ. የእግዚአብሔርን ቃል ማጣመም - (ሐዋ. 13:10፣ 2ጴጥ. 2:14)

ለ. ክፉ ሥራ - (ምሳ. 17:20-23)

ሐ. ክህደት (atheism) - (ሮሜ.1:30፣ ምሳ. 14:2)

መ. የስህተት ትምህርት - (ኢሳ. 19:14፣ 2ጢሞ. 3:7-8 ፣ ሮሜ.1:22-23)

ሠ. የማይገባ የግብረ ሥጋ ግንኙነት - (ሮሜ. 1:17-32፣ 1ቆሮ. 6:9፣ 1ጢሞ. 4:2)

ረ. ጽንስን ማስወረድ እንደተገቢ ነገር መቁጠር - (ዘጸ. 21:22-25 የመሳሰሉት ናቸው።

*"ክፉንም መልካም መልካሙንም ክፉ ለሚሉ ጨለማውን ብርሃን ብርሃኑንም ጨለማ ለሚያደርጉ ጣፋጩን መራራ መራራውንም ጣፋጭ ለሚያደርጉ ወዮላቸው" (ኢሳ. 5:20)*

*"የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሳውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ..." (2 ቆሮ. 10:5)*

### 6. የትዕቢት መንፈስ

*"ትዕቢት ጥፋትን ኩሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል ..." (ምሳ. 16:18)*

ትዕቢት የተቀባውን ኪሩብ ወደ ሰይጣንነት የለወጠ ክፉና አስፈሪ ኃጢአት ነው።

*"ከፍ ያለችውም የሰው ዓይን ትዋረዳለች፣ የሰዎችም ኩራት ትወድቃለች፣ በዚያም ቀን እግዚአብሔር ብቻውን ከፍ ከፍ ይላል።" (ኢሳ. 2:11)*

ጣዖትን ማምለክ አጋንንትን ማምለክ ነው። (መዝ. 106:36-38) የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመቃወም አጋንንት ከሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች መካከል ዓለማዊ የሆኑ ሃይማኖቶችን በማብዛት ነው። ይህም በምትሐት፣ በጥንቆላ፣ በመተት ተብትበው ሰዎችን በማስር ነው።

> *"የባለቤቱም ባሮች ቀርበው:- ጌታ ሆይ፥ መልካምን ዘር በእርሻ ዘርተህ አልነበረምን? እንክርዳንዱንስ ከወዴት አገኘ? አሉት። እርሱም:- ጠላት ይህን አደረገ አላቸው።" (ማቴ. 13:27-28)*

## 3. ሰዎችን መጨቆን (Opperssing Mankind)

አጋንንት እግዚአብሔርንና በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረውን ሰው እጅግ ይጠላሉ። የተቻላቸውን ያህል ሰዎችን ወደ ገሀነመ እሳት ይጎትታሉ። ሰዎች እውነተኛ ሰላምና ደስታ የሚሰጠውን የእግዚአብሔር ጸጋ ይኸውም ክርስቶስ ኢየሱስን እንዳያውቁ አምነውም እንዳይድኑ አእምሮአቸውን ያሳውራሉ። (2ቆሮ. 4:3-4) በጸጋ ፈንታ ሰው በሃይማኖታዊ ሥርዓት ብቻ እንዲያዝና ዓለምን እንዲወድ ያደርጋሉ። (ገላ. 3:1-3 1፣ 1ጢሞ. 4:1-8)

ሌላው በሰዎች ላይ የሚያመጡት ተጽዕኖ ሰውን በዲዳነት፣ በድንቁርና (ማቴ. 9:32-33)፣ በአይነ ስውርነት (ማቴ. 12:22)፣ በማጉበጥ (ሉቃ. 13:11-17) እና በተለያዩ በሽታዎች ማጥቃት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉም በሽታ በአጋንንት ምክንያት ነው አይልም ነገር ግን ግልጽ አድርጎ ከአጋንንት የሆነውንና ያልሆነውን ይናገራል። (ማቴ. 4:24፣ ሉቃ. 7:21)

አጋንንት ሰው ራሱን መርዝ እንዲጠጣ፣ ከፎቅ እንዲወድቅ፣ በገመድ እንዲታነቅ፣ በሚጎዳና በሚያሰጥም ነገር ውስጥ ራሱን እንዲጥል ይገፋፉታል (ማር. 5:5, 9:22) ሌሎችንም እንዲያጠፉና እንዲገድሉ ይገፋፉታል። (ራዕ. 18:2, 24) አጋንንት በቀጥታ ሰዎችን ይገድላሉ። (ራዕ. 9:14-19)

## 4. በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉትን መቃወም

የሰይጣን ዋና ዒላማ አማኞች ነን። ምክንያቱም በሥጋ ተገልፆ ሥራውን ያፈረሰው፣ በሞቱና በትንሳኤው ደግሞ ራሱን የቀጠቀጠው፣ የክርስቶስ ኢየሱስ አካል ስለሆንን ነው። ይህም:-



### ሀ. የወንጌልን ስብከት በመቃወም

ክርስቲያኖች የምንሰብከውን የእውነትን ወንጌል ሰዎች እንዳይሰሙት፣ እንዳይቀበሉት በማድረግ ወይንም በሚጣመም ሲሆን (ሉቃ. 8:12)፣ የሰዎችን አዕምሮ በማጨለም፣ (2 ቆሮ. 4:3-4) የወንጌል አገልጋዮች በሰይጣን ግዛት ውስጥ ያሉትን በወንጌል እውነት ነጻ እንድናወጣ ከጉዞአችን ማዘግየትና ፊት ለፊት በመቃወም ነው። (1ተስሎ. 2:18)

### ለ. የቅዱሳንን ትዳር፣ ቤተሰብና ኑሮ(ሥራ) በመቃወም

አጋንንት አማኞችን በቀጥታ ይዋጋሉ። ይህም ውጊያ እንደ ጨበጣ ውጊያ እንደሆነ በኤፌ. 6:12 ላይ ተገልጾአል። የምንዋጋውም ከደምና ከሥጋ (ከሰዎችም) ጋር አይደለም ነገር ግን ከአለቆችና ከሥልጣናት ከዚህ ዓለም ጨለማ ገዢ መናፍስትና በአየር ላይ ካሉ ከክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት ጋር ነው። እነዚህ መናፍስት በኤፌ. 5 እና 6 እንደተገለጸው የክርስትያንን ትዳር፣ ቤተሰብና ሥራ የሚዋጉ ናቸው። ይህ ውጊያ እንደ ጨበጣ ውጊያ በመሆኑ ክርስቲያን ሁሉ ድል በክርስቶስ ኢየሱስ የእርሱ መሆኑን አውቆ መዋጋት አለበት። (ሮሜ 8:35-39)

### ሐ. ቅዱሳንን በእግዚአብሔር ፊት በመክሰስ

ክርስቲያኖች በሕይወታችንና በአገልግሎታችን እንዳንበረታ ሰይጣን በእግዚአብሔር ፊት ቀንና ሌሊት ይከሰናል። (ራእ. 12:10) በዘካ. 3:1-2 ታላቁ ካህን ኢያሱን ያደፈ ልብስና በራሱም መጠምጠሚያ አድርጎ በእግዚአብሔር ፊት በቆመ ጊዜ ሰይጣን ከሰሰው። እግዚአብሔር ሰይጣንን ገስፆ ኢያሱን አዲስ ልብስና አዲስ መጠምጠሚያ እንዲያደርጉለት አዘዘ። አዲስ ቃልኪዳንም ገባለት።

እኛ አማኞች እናገለግላለን፣ ሥራ እንሰራለን፣ እንበላለን፣ እንጠጣለን፣ እንተኛለን። ሰይጣን ግን ቀንና ሌሊት ወንድሞችን ይከሳል። ነገር ግን የማይተኛና የማያንቀላፋ እረኛችን እግዚአብሔር ሰይጣንን ስለሚገስጽ በዚህ ደስ ይለናል። ወንድሜ ሆይ ቀንና ሌሊት የዲያብሎስን ክስ ከምታስላስል በቀንም በሌሊትም የእግዚአብሔርን ቃል አስብ። (ኢያሱ 1:7-8)

ሰይጣን «አንተን(አንቺን) ብሎ አገልጋይ፣ አንተን (አንቺን) ብሎ ክርስቲያን» ቢልህ አትቀበለው። ደግሞስ ከመቼ ወዲህ ነው ሰይጣን ስለአገልግሎትህና ስለሕይወትህ ተቆርቋሪ የሆነው?

ሰይጣን ጠላታችን ስለሆነ ይከሰናል መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ወዳጃችን ስለሆነ ይወቅሰናል። መንፈስ ቅዱስ ሲወቅሰን ወደ ንስሐ ይመራናል። የሰይጣን ክስ ግን ከእግዚአብሔር ያርቀናል። ሰይጣንን እንገስጸው መንፈስ ቅዱስን ግን እንቀበለው።

መ. አማኞች የእግዚአብሔርን በጎነት፣ ቸርነት፣ ምህረትና እውነት እንዲጠራጠሩ ማድረግ። (ዘፍ. 3:1-5)

ሠ. አጋንንት ክርስቲያናችን በኃጢአት ይፈትናሉ

ይህም በግብዝነት፣ በውሸት፣ በርኩሰት (ሐዋ. 5:3-1፣ 1ቆሮ. 7:5)፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ በራሳቸው ጥበብና ኃይል እንዲመኩ (1 ዜና 21:1-8፣ ማቴ. 16:21-23) በመንፈሳዊ ነገር እንዲታበዩ (1 ጢሞ. 3:6) እና በመጠን እንዳይኖሩ በማድረግ (1 ጴጥ. 5:6-10) ነው።

ልብ ማለት ያለብን በኃጢአት መፈተን ምንጩ አጋንንት ብቻ እንዳልሆኑ ነው። አንድ ክርስቲያን የቅድስና ሕይወት ከሌለውና እንደ ቃሉ የማይኖር ከሆነ በገዛ ምኞቱ ሲሳብና ሲታለል ይፈተናልና። (ያዕ. 1:14)

ረ. አጋንንት ስደትን ያመጣሉ (ራእ. 2:10)

ሰ. አጋንንት የክርስቶስ ኢየሱስን ቤተክርስቲያን ለማድከም ይተጋሉ

ይህም:-

* የብርሃን መልአክ መስለው ነገር ግን የሰይጣን መልዕክተኞች በሆኑ በስህተት አስተማሪዎች በመጠቀም (2 ቆሮ. 11:13፣ 15:1፣ 1ጢሞ. 4:1-5)
* የስህተት ትምህርት በማምጣት (1 ዮሐ. 4:1-4)
ክርስቲያኖች ዓለማዊና አስመሳይ ሕይወት እንዲኖሩ በማድረግ (ቆላ. 2:18-23) በጤናማው የቃሉ ስንዴ እንክርዳድን በመዝራትና ክርስቲያኖችን ግራ በማጋባት ሲሆን (ማቴ. 13:38-39) በቤተክርስቲያንም አለመግባባትና መከፋፈልን ያመጣሉ። ይህም ቁጣን፣ ንዴትንና ትዕቢትን በመዝራት ነው። (ኤፌ.4:26-27)

ሸ. ለክርስቶስካለን ፍቅር፣ ቅንዓትና ንጽህና ሊለዩን ይተጋሉ (2 ቆሮ. 11:3)

ቀ. ከአጋንንት ማህበራት ጋር ማመቻመች (Compromising) እንዲኖር ያደርጋሉ (1ቆሮ. 10: 20-21)

በ. ተስፋ ያስቆርጣሉ

በዘሩባቤል ፊት ታላቅ የተስፋ መቁረጥ ተራራ ነበረ እግዚአብሔር ተራራውን ገስጸው።



# ምዕራፍ አምስት
# የሰይጣንና የአጋንንት ሽንፈት

ሰዎችን ከአጋንንት እስራትና መገዛት ነጻ ለማውጣት ሰይጣንና አጋንንት በክርስቶስ ኢየሱስ እንደተሸነፉና አለቅነታቸውና ሥልጣናቸው እንደተገፈፈ ማስተዋል ተገቢ ነው።

ሰው በኃጢአት በወደቀ ጊዜ እግዚአብሔር የሰጠውን ዓለምን የመግዛት ሥልጣኑን አጣ። (ዘፍ. 1:26 3:7-9) ሰይጣንም የዚህ ዓለም ገዢ ሆነ (ዮሐ. 14:30፣ 2 ቆሮ. 4:4፣ 1 ዮሐ. 5:19)

ጌታ ኢየሱስ ሰይጣንን ድል በመንሳት ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንዲመለስና ከዚያም በላይ ወደ ሆነው ሥልጣን እንዲገባ አዳኝ ሆነ። (ማቴ. 4:1-11 ዕብ. 10:38) ይህም በአገልግሎቱ በአጋንንት የተያዙትንና የታሰሩትን ነጻ እያወጣ ድል አድራጊነቱን ይገልጽ ነበር። (ማቴ. 8:16-32 9:33 12:28) በተጨማሪም አጋንንት እንዲያወጡ ደቀ መዛሙርቱን ሾማቸው (ማቴ. 10:1 ማር. 3:14-15) ሰባዎቹም በክርስቶስ ኢየሱስ ስም አጋንንት ሲታዘዙላቸው በደስታ ተሞሉ (ሉቃ. 10:17-20) በመስቀል ላይ በሠራው ሥራ አለቅነታቸውንና ሥልጣናቸውን ገፎ በግልጽ እየዞረ አሳያቸው። (ቆላ. 2:14-15) በመስቀል ላይ የዚህ ዓለም ገዢ ተፈረደበት (ዮሐ. 12:31-33) ጌታ ኢየሱስ በሞቱ ዲያብሎስን ራስ ቀጥቅጦ ነጻነትን አወጀልን። ሃሌሉያ!

በአሁኑ ጊዜ ክርስቶስ ኢየሱስ በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ታላቅ ስም ወርሶ የክብርንና የምስጋናን ዘውድ ተጭኖ ከአለቆችና ከሥልጣናት፣ ከዙፋናትና ከጌትነት ሁሉ በላይ ነው። አሜን።

በሰማይና በምድር ሥልጣን ያለው ኢየሱስ ነው። በምትኖርበት አገር፣ በአፍሪካ፣ በሰሜን አሜሪካ፣ በደቡብ አሜሪካ፣ በማርስ፣ በጁፒተር፣ በፀሀይ፣ በጨረቃ በከዋክብት ... ሁሉ ሥልጣን የኢየሱስ ነው።

አንድ የአሜሪካ ትራፊክ ፖሊስ በአሜሪካ ሀገር መኪናዎች የማስቆም ሥልጣን አለው። ሥልጣኑ በአሜሪካ መንግሥት ሕግ የተሰጠው ነው ወደ ኢትዮጵያ ቢመጣ ግን ሥልጣኑ አይሠራም። እኛ ዳግም የተወለድን ግን በኢስያ፣

አይችሉም። (1 ቆሮ. 2:15) አጋንንት ብዙ እንዲናገሩ መፍቀድ ግን ተገቢ አይደለም።

## ሠ. በሰውዬው ሰውነት ላይ ጉዳት ማድረስ

*"ርኩሱም መንፈስ አንፈራገጠውና በታላቅ ድምጽ ጮሆ ከእርሱ ወጣ።" (ማር. 1:26)*

"ከዚያም በኋላ ጋኔን ያደረበትን ዕውር ዲዳም ወደ እርሱ አመጡ።" (ማቴ. 12:22)

ይህም ማንፈራገጥ፣ መጮህ፣ ዲዳነት፣ ዕውርነት፣ ሰውነትን መቧጨር፣ ሌሎችን መምታት፣ ዕቃ መሰባበርን ያካትታል። እነዚህ ምልክቶች በሰውነት በሚፈጠረው የኬሚካል መለዋወጥ ሊፈጠሩም ስለሚችሉና በተለይም ደግሞ ዲዳነትና፣ እውርነትና የመሳሰሉት በሽታዎች ሌላ ምንጭ ሊኖራቸው ስለሚችል እንድ ሰው ዓይነ ስውር ወይም ዲዳ ሆነ ማለት አጋንንት ያዘው ማለት አይደለም። ስለዚህም መለየት አስፈላጊ ነው።

## ረ. ራስን መጉዳትና ማጥፋት

*"ብዙ ጊዜም ሊያጠፋው ወደ እሳትም ወደ ውኃም ጣለው ... " (ማር. 9:22)*

*"... ሌሊትና ቀን በመቃብርና በተራራ ሆኖ ይጮህ ነበር ሰውነቱንም በድንጋይ ይቧጭር ነበረ ።" (ማር. 5:5)*

- በውኃ፣ በገደልና በእሳት መጣል፣ መርዝ ማጠጣት፣ከፎቅ ራስን መጣል ይህ በአጋንንት ግፊት ሲሆን ዓላማውም ሰውዬውን ለማጥፋት ነው።
- ከቤት ውጪ ማሳደር (በመቃብርና ሰው በማይኖርበት)
- ራስን መጣል
- ሌሎችን መረበሽ የመሳሰሉ ናቸው።



## ሰ. የጌታ ስም ሲጠራ መፍራትና መረበሽ

*"እርሱም የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ ከአንተ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን መጣህን? ማን እንደሆንህ አውቄአለሁ የእግዚአብሔር ቅዱሱ ብሎ ጮኸ።" (ማር. 1:24)*

አጋንንት ያደሩባቸው ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃልና የኢየሱስ ክርስቶስን ስም፣ በመስቀሉ ላይና በትንሳኤው የተሠራውን ሥራ መስማት አይወዱም ይፈራሉ፣ ይጮሃሉ።

# 6.1.3 አጋንንት በሰው ውስጥ የማደራቸው መጠን (Degree of Demonization)

ባለፉት ገጾች አጋንንት በሰው ውስጥ ሲያድሩ የሚኖራቸውን ምልክት ተመልክተናል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረንና ከልምድ እንደምናየው አጋንንት በሰው ውስጥ ሲያድሩ መጠን (Degree) አላቸው። ይህም መጠን በሦስት ዓይነት መንገድ ይለያያል። ይኸውም:-

### ሀ. <u>በአጋንንቱ ክፋት</u>

አጋንንት ሁሉ ክፉዎች ቢሆኑም የከፋታቸው መጠን ይለያያል።

*"ርኩስ መንፈስ ግን ከሰው በወጣ ጊዜ እረፍት እየፈለገ ውኃ በሌለበት ቦታ ያልፋል አያገኝምም። በዚያን ጊዜም ወደ ወጣሁበት ቤት እመለሳለሁ ይላል ቢመጣም ባዶ ሆኖ ተጠርጎና አጊጦ ያገኘዋል። ከዚያ ወዲያ ይሄድና <u>ከእርሱ የከፉትን</u> ሌሎች አጋንንትን ከእርሱ ጋር ይወስዳል ገብተውም በዚያ ይኖራሉ ለዚያም ሰው ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው ይብስበታል ለዚህ ክፉ ትውልድ ደግሞ እንዲሁ ይሆንበታል።" (ማቴ. 12:44-45)*

### ለ. <u>በአንድ ሰው በሚያድሩት የአጋንንት ብዛት</u>

ለምሳሌ በማር. 5 ላይ የምንመለከተው ሰው የያዘው ሌጊዎን (3000-6000) አጋንንት ሲሆኑ መግደላዊት ማርያምን የያዟት ግን ሰባት ነበሩ።

### ሐ. <u>በአጋንንቱ የኃይል አሰላላፍ</u>

አጋንንት በሥልጣን አንዳቸው ከሌላቸው ይበላለጣሉ። በሰውዬው ውስጥ የገቡት መናፍስት ባለሥልጣናቱ ከሆኑ የተደራጁ ናቸው ማለት ነው። እነዚህን ለማውጣት በኅብረት መጸለይና መጾም አስፈላጊ ነው።

## 6.2 በአጋንንት መጨቆን (Demonic Opression)

አጋንንት በሰው ውስጥ እንደሚያድሩ (Demonic Possession) ቀደም ሲል ተመልክተናል። አጋንንት በሰው ውስጥ ማደር ካልሆነላቸው ሁለተኛ የከፋት ዘዴአቸው ማሰር፣ ፍላጻቸውን መወርወርና መውጋትና የሰውዬው

የሆነውን ነገር መያዝ (ማሰር) ነው። ይህ ደግሞ የአጋንንት ጭቆና (Demonic Oppression) ይባላል።

ዳግም የተወለደ ክርስቲያን ውስጥ አጋንንት መግባት አይችሉም። ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጡ ስለሚኖር የእግዚአብሔርም መቅደስ ሆኗልና። ነገር ግን የእምነትን ጋሻ ካላነሳ፣ በቅድስና ካልኖረ፣ የጸሎት ሕይወት ከሌለውና ዲያብሎስን ጸንቶ ካልተቃወመ አጋንንት የሚንበለበሉ ፍላጻዎቻቸውን በመወርወር ሊያጠቁት ስለሚችሉ በአጋንንት ከውጭ (Externaly) ሊጨቆን ይችላል። ስለዚህ ነው ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ማንሳትና መልበስ ያለበት።

> *"የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና ..." (ኤፌ. 6:11-12)*

### 6.2.1 የአጋንንት ጭቆና በምን ሊመጣ ይችላል?

ጭቆና በተለያየ ዓይነት መንገድ ሊመጣ ይችላል እነርሱም:-

### 1. በመናፍስት ዓለም በመሳተፍ

አንድ ሰው ቀደም ሲል በመናፍስት ዓለም ውስጥ ከነበረ ማለትም ወደ ጠንቋይ ቤት መሄድ መስተፋቅር፣ ድግምት፣ ራምፓ፣ ዮጋ ወዘተ ውስጥ ከተሳተፈ ወይንም በእርሱ ላይ ከተደረገበት በአጋንንት ይታሰራል። ይህም እስራት መንፈሳዊ ዓይንን ያጨልማል፣ የልብ ጆሮን ይዘጋል፣ ለመንፈሳዊ እውነት አለመታዘዝን ያመጣል፣ መጻለይን ዳገት ያደርገዋል፣ ቅዠትና መጫጫን፣ በተጨማሪም በኑሮ አለመሳካትን ሊያስከትል ይችላል።

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 እንደምናነበው ሲሞን የሚባል ቀደም ሲል ጠንቋይ የነበረ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን አምኖ ተጠመቀ ነገር ግን ከእስራት ነጻ አልወጣም ነበርና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በገንዘብ ሊያገኝ ተመኘ ለመነም።



> *" ... የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ እንድታገኝ አሰበሃልና ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፋ። ልብህ በእግዚአብሔር ፊት የቀና አይደለምና ከዚህ ነገር ዕድል ወይም ፈንታ የለህም። እንግዲህ ስለዚህ ክፋትህ ንስሐ ግባ ... በመራራ መርዝና በአመጽ እስራት እንዳለህ አይሃለሁና። " (ሐዋ. 8:20-23)*

ሰዎች አጋንንት ከወጡላቸው በኋላ አጋንንቱ ተመልሰው በእስራት እንዳያጠቋቸው የሰይጣን መሣሪያ የሆኑትን እንደ ክታብ፣ ጨሌ፣ የጥንቆላ

መጻሕፍትና የተደገመባቸውን ልብሶች በሰው ፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ስም ከደው ማቃጠል ያስፈልጋቸዋል።

> *"የጌታም ኢየሱስ ስም ተከበረ አምነውም ከነበሩት እጅግ ሰዎች ያደረጉትን እየተናዘዙና እየተናገሩ ይመጡ ነበር። ከአስማተኞችም ብዙዎቹ መጽሐፋቸውን ሰብስበው በሰው ፊት ሁሉ አቃጠሉ ዋጋውም ቢታሰብ ሃምሳ ሺህ ብር ሆኖ ተገኘ። እንዲሁም የጌታ ቃል በኃይል ያድግና ያሸንፍ ነበር።" (ሐዋ. 19:18-19)*

### 2. ኃጢአትን በድፍረት መለማመድ

ይህ ኃጢአትን በድፍረት መለማመድ አንድን ክርስቲያን ለአጋንንት ጭቆና ሊዳርገው ይችላል። እስራት ውስጥ ከገባ ደግሞ ያ ኃጢአት ሱስ ይሆንበታል። ይህም:-

ሀ. በዝሙትና ሴሰኝነት

> *"... ወዳጆች ሆይ ስለምንካፈለው ስለመዳናችን ልጽፍላችሁ እጅግ ተግቼ ሳለሁ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ስለተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ። ከብዙ ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ አንዳንዶች ሰዎች ሾልከው ገብተዋልና ኃጢአተኞች ሆነው የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኝነት ይለውጣሉ ንጉሣችንና ጌታችንንም ብቻውን ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ።" (ይሁዳ 3-4)*

የእግዚአብሔር ጸጋ ሰዎችን ሁሉ የሚያድንና ዓለማዊ ምኞትን የሚያስክድ ወይም የሚያስጥል እንጂ ለዝሙትና ለሴሰኝነት መከታ አይደለም። በሴሰኝንነት ምክንያት ከሚመጣው ፍርድ በጌታ ጸጋ ማምለጥ ብልኅነት ነው።

> *"ዳሩ ግን ሁሉን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ምንም የተማራችሁ ብትሆኑ ጌታ ከግብጽ አገር ሕዝቡን አድኖ የማያምኑትን በኋላ እንዳጠፋቸው ላሳስባችሁ እወዳለሁ። መኖሪያቸውንም የተውትን እንጂ የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁትን መላእክት በዘላለም እስራት ከጨለማ በታች እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ ጠብቆአቸዋል። እንዲሁም እንደ እነርሱ ዝሙትን ያደረጉና ሌላን ሥጋ የተከተሉ ሰዶምና ገሞራ*

*በሁሪያቸውም የነበሩ ከተማዎች በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል።" (ይሁዳ 5- 7)*

ዝሙት መሥራት የዘለዓለም መኖሪያ የሆነው እግዚአብሔርን መተውና እግዚአብሔር የሰጠንን መንፈሳዊ ሥልጣን መጣስ ሲሆን በዘለዓለም እስራት ከጨለማ በታች ውስጥ ካሉ አጋንንት ጋር መተባበርን ያሳያል። ለዚህ ነው ይህ የኃጢአት ልምምድ እስራትን የሚያመጣው።

*"እንዲሁም እነዚህ ሰዎች ደግሞ እያለሙ ሥጋቸውን ያረክሳሉ ጌትነትንም ይጥላሉ ሥልጣን ያላቸውንም ይሳደባሉ። የመላእክት አለቃ ሚካኤል ግን ከዲያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ ስለ ሙሴ ሥጋ ሲነጋገር ጌታ ይገስጽህ አለው እንጂ የስድብን ፍርድ ሊናገር አልደፈረም እነዚህ ግን የማያውቁትን ሁሉ ይሳደባሉ አእምሮ እንደሌላቸው እንስሶች በፍጥረታቸው በሚያውቁት ሁሉ በእርሱ ይጠፋሉ።" (ይሁዳ 8-10)*

*" ... እትላቱ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።" (1 ቆሮ. 6:9-10)*

የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅ ሰላም በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ደስታ ናት። ኃጢአትን የሚለማመድ በእስራት ውስጥ ስላለ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም።

*"ራሳቸው የጥፋት ባርያዎች ሆነው አርነት ትወጣላችሁ እያሉ ተስፋ ይሰጡአችኋል ሰው ለተሸነፈበት ለእርሱ ተገዝቶ ባርያ ነውና። በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ከዓለም ርኩሰት ካመለጡ በኋላ ዳግመኛ በእርሷ ተጠላልፈው የተሸነፉ ቢሆኑ ከፊተኛው ኑሮአቸው ይልቅ የኋለኛው የባሰ ሆኖባቸዋል።" (2 ጴጥ. 2:19-20)*

በራዕይ 21:8 ላይ ሴሰኞች ከማያምኑ፣ ከርኩሳን ከነፍስ ገዳዮች፣ አስማተኞችና ጣዖትን ከሚያመልኩ ጋር ተመድበዋል።

*"ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኩሳንም የነፍሰ ገዳዮችም የሴሰኞችም የአስማተኞዎችም ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኞዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛ ሞት ነው።"*



ከጋብቻ ውጪ የሆነ የግብረሥጋ ግንኙነት ማድርግ፣ የርኩሰት መጻሕፍት ማንበብና በብልግና የተሞሉ ፊልሞች ማየት (Pornography)፣ መዳራት፣ ከማያምኑም ጋር በማይመች አካሄድ መጠመድ እስራትን ያመጣል።

ሰ. በዓመፀኝነት

*"ዓመፀኝነት እንደ ምዋርተኛ ኃጢአት፥ እልከኝነትም ጣዖትንና ተራፊምን እንደ ማምለክ ነው... " (1 ሳሙ. 15:23)*

በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ፣ እግዚአብሔርን ቸል ብሎ ሰይጣንን (ምዋርትን) መከተልና ጣዖታትን ማምለክ ነው። ከዓመፅና ከአለመታዘዝ በስተጀርባ ዓመፀኛ የሆነውና ባለመታዘዙ የተጣለው ሰይጣን አለ።

ንጉሥ ሳኦል ተቀብቶ እያለ ዓመፀኛ ነበር። በመጨረሻ እግዚአብሔር ቅባቱን ከእርሱ ባነሳ ጊዜ (መንግስቱን ሲወስደው) ሳኦል በእስራት ውስጥ ገባ። የንጉሥነት ቅባት ሲርቀው ከፉ መንፈስ ያስቃየው ጀመር። ዳዊት ይህንን ስላየ ነው። በመዝ. 51:10-11

*"አቤቱ፥ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፥ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ። ከፊትህ አትጣለኝ፥ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ።"* ብሎ የጸለየው።

ማመጽ የመንፈስ ቅዱስ ቅባትን ከሕይወት ያርቃል። በእስራት ውስጥ ያስገባል።

*" ... የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከዓመፅ ይራቅ ..."(2 ጢሞ. 2:19)*

ሐ. በትዕቢት

*"በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ፥ አዲስ ክርስቲያን አይሁን። በዲያብሎስ ነቀፋና ወጥመድም እንዳይወድቅ፥ በውጭ ካሉት ሰዎች ደግሞ መልካም ምስክር ሊኖረው ይገባዋል።" (1 ጢሞ. 3:6-7)*

ትዕቢት የተቀባው ኪሩብን ወደ ሰይጣንነት የለወጠ የልብ ኃጢአት ነው። ይህ እስራት የእምልኮን መልክ ያስይዛል የእግዚአብሔርን ኃይል ግን ያስክዳል። ይህ ደግሞ ሕይወት ሰጪ የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ ሕይወትን ከመለወጥ የሚከለክልና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በቤተክርስቲያን እንዳይገለጹ ወይም ሰዎች እንዳይለማመዱ ያደርጋል።

መ. ይቅርታ ባለማድረግ

*"እናንተ ግን ይቅር የምትሉትን እኔ ደግሞ ይቅር እለዋለሁ እኔም ይቅር ካልሁ÷ ይቅር ያልሁትን ስለ እናንተንም በክርስቶስ ፊት ይቅር ብዬአለሁ ..." (2 ቆሮ. 2:10-11)*

*"ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ እናንተንም ደግሞ ይቅር ይላችኋልና ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም ።" (ማቴ. 6:14-15)*

እግዚአብሔር ምህረቱ ለዘለዓለም ይቅርታውም የበዛ አምላክ ነው። ሰይጣን ደግሞ ምህረት የሌለው ክፉ ፍጥረት ነው። ይቅርታ የእግዚአብሔር ባህርይ በመሆኑ ይቅር አለ'ለት ደግሞ የሰይጣን ባህሪ ስለሆነ መንፈስ ቅዱስን ያሳዝነዋል። ሰይጣንን ግን ስደስተዋል እስራትንም ያመጣል።

*"ለሚሰሙት ጸጋን ይሰጥ ዘንድ÷ እንደሚያስፈልግ ለማነጽ የሚጠቅም ማናቸውም በጎ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ። ... እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ።" (ኤፌ. 4:29-32)*

## 3. በሥጋ ሥራዎች

ብዙውን ጊዜ የአጋንንት እስራት ከሥጋ ሥራዎች ጋር የተያያዘ ነው።

*"የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንዓት፣ ቁጣ፣ አድመኛ ነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም። " (ገላ. 5:19-21)*

ሥጋ በመስቀሉ ኃይል ከክፉ ምኞቱና አሳቡ ጋር ከተሰቀለ ነጻነት አለ።

*"የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑትም ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።"* (ገላ. 5:24)

## 4. በመርገም

የአጋንንት እስራት ከመርገም ሊመጣ ይችላል። መንፈስ ከሚተላለፍባቸው መንገዶች አንዱ ቃል በመናገር ነው። ስለዚህ ንግግር ሞት ወይም ሕይወት፣ ክፉ ወይም መልካም፣ መርገም ወይም በረከት ሊሸከም ይችላል። (ምሳ. 18:21)



መርገም በሰዎች ላይ ክፉ ነገር እንዲደርስባቸው የሚነገር ክፉ ንግግር ሲሆን የሚከናወነው በአጋንንት ነው። የመርገም ምንጮች፡- የእግዚአብሔርን ሕግ በመተላለፍ የሚመጡ ሲሆኑ

ሀ. በወላጅ የሚመጣ መርገም

*"ሕዝቡም ሁሉ መልሰው ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን አሉ።"* (ማቴ. 27:25) ዘጸ. 20:4-5

እስራኤላውያን የኢየሱስ ደም በእኛና በልጆቻችን ይሁን በማለታቸው በራሳቸውና በዘራቸው የመጣው መርገም ቀላል እንዳልሆነ በእስራኤልና በጀርመን እንዲሁም ደግሞ በዓለም ዙሪያ ከደረሰባቸው ነገር መረዳት ይቻላል።

ለ. በራስ የሚመጣ መርገም

*"ሕዝቡም ሁሉ መልሰው ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን አሉ።"* (ማቴ. 27:25)

ሐ. በሌሎች የሚደረግ መርገም (ኢያሱ 6:26፣ 1 ነገስ. 16)

መ. ከእግዚአብሔር የሚመጣ መርገም

በዘዳ. 27 መሠረት ጣዖትን የሚያመልክ፣ የተቀረፀን ምስል ለራሱ የሚያደርግ፣ ባልጀራውን የሚበድል፣ ዕውሩን ከመንገድ ፈቀቅ የሚያደርግ (ደካማውን የሚያጠቃ)፣ ከአባቱ ሚስት፣ ከእናቱ ልጅ ከእህቱ፣ ከአማቱ፣ከማናቸውም እንስሳ ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚያደርግ፣ ባልንጀራውን በስውር የሚመታ፣ የንጹህ ሰው ነፍስ ለመግደል ጉቦ የሚቀበል እና የእግዚአብሔርን ቃል ያደርግ ዘንድ በማይጸና ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር መርገም ይመጣል።

ይህ ማለት የእግዚአብሔርን ቃል በመተላለፍ በተደጋጋሚ በሚበድሉት ላይ እግዚአብሔር ጥበቃውንና በረከቱን ያነሳል ማለት ነው።

ሠ. በአጋንንት የሚመጣ መርገም

ይህ መርገም አጋንንት ባለባቸው በሟርተኞች፣ አስማተኞችና ጠንቋዮች የሚመጣ ነው። ዘኁ. 22:6፣ 23:7፣ ዘዳ. 11:26-28፣ መሳ. 5:2

## 6.2.2 አጋንንት ሰውን የመጨቆናቸው መጠን

## (Degree of Oppression)

አጋንንት ሰውን የመጨቆናቸው መጠን በአራት ደረጃ ይከፈላሉ።

*1. በሚንበለበሉ ፍላጻ መወጋት*

*2. ለሰይጣን ፈንታ መስጠት (Footholds)*

*3. ምሽግ (Strongholds)*

*4. እስራት (Bondages)* ናቸው እነዚህ አራቱን በዝርዝር እንመለከታቸው:-

### 1. የሚንበለበሉ ፍላጻዎች

*"በእውነት ታጥቃችሁ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉ ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ።" (ኤፌ. 6:15-16)*

እነዚህ ፍላጻዎች የሚንበለበሉ ስለሆኑ አንድ ሰው የእምነትን ጋሻ አንስቶ መመከት ሲገባው ሳይመከት ሲቀር የሚወጉት ናቸው። እነዚህ ፍላጻዎች ከፉዎች ቢሆኑም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይነቀላሉ።

### 2. ለጠላት ፈንታ መስጠት (Footholds)

*" ... ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት" (ኤፌ. 4:17-32)*

ይህ የጭቆና ዓይነት እንደ አሕዛብ በኃጢአት በመመላለስ ቅድስና የሌለው ኑሮ ይህም ዝሙት፣ ሴሰኝነት፣ ኃጢአት ያለበት ቁጣ፣ ውሸት፣ መስረቅ ወዘተ ውስጥ በመግባት የሚመጣ ነው።

### 3. ምሽግ (Strongholds)

*"በሰው ልማድ ምንም የምንመላለስ ብንሆን እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሳውን ከፍ ያለውን ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስ ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን መታዘዛችሁም በተፈጸመች ጊዜ አለመታዘዝን ሁሉ ልንበቀል ተዘጋጅተናል።" (2 ቆሮ. 10:3-6)*



ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው የሰው አሳብ ማለት በእግዚአብሔር እውቀት ላይ የሚነሳ፣ የሚያምጽ፣ ከፍ ያለ ነገር፣ እኔ እበልጣለሁ ወይንም የኔ አሳብ ከእግዚአሔር ፈቃድ ይበልጣል የሚል አሳብ ነው። ይህ ደግሞ በእግዚአብሔር ሥልጣን ላይ ባመጸው ከሰይጣን የሚመጣ ነው። ይህን ደግሞ ዲያብሎስ እንደ ምሽግ ይጠቀምበታል።

ምሽጉ ያለው በአሳብ ውስጥ ነው አንዳንድ ጊዜ ምሽጎች ጥሩና መልካም አሳቦች የሚመስሉ የሰው አሳቦች ናቸው (ማቴ. 16:21-23) በውስጣችን የልብ ቁስል ሊቀሰቅሱ የሚችሉና ሰውን ወላዋይ የሚያደርጉ ናቸው። (ያዕ. 1:8)

### 4. እስራት (Bondage)

አንድ ሰው በተለያየ የመናፍስት ዓለማት ከተሳተፈ ወይም መተት፣ አስማት ወዘተ ሲደረግበት የሚመጣ ነው።

## *6.2.3 በአጋንንት የመጨቆን ምልክቶች*

የአጋንንት ተጽዕኖ ደረጃቸውን ተመልክተናል። በእነዚህ ደረጃዎች መሠረት ወደ መጽሐፍ ቅዱሳችን ስንሄድ :-

- ሰው በፍላጻ ከተወጋ ኤፌ. 5 እና 6 ባለው መሠረት ስንመለከት በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ያቅተዋል፣ ለእግዚአብሔር መዘመር፣ በነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ማመስገን፣ ሚስት ለባል መገዛት፣ ባል ሚስቱን መውደድ፣ ልጆች ወላጆቻቸውን ማክበር ይሳናቸዋል። እንዲሁም ወላጆች ልጆቻቸውን መቆጣት፣ በሥራ ቦታ ታማኝ አለመሆንና አሠሪም ከሆኑ ሠራተኞችን መበደል ያመጣል። ፍላጻ ይህንን ሁሉ ስለሚያስከትልብን ነው በኤፌ. 6:10-18 ሰይጣንን ተዋጉ የሚለን።

እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን እነዚህ ችግሮች ከራሳችን ድካም፣ ልጆችም በአከባቢያቸው ከሚማሩትና ከአስተዳደግ ሊመጡ እንደሚችሉና ወዘተ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ።

- ሰው ለሰይጣን ፈንታ ከሰጠ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን፣ ዝሙት፣ ሴሰኝነት ይነግሥና አሮጌው ሰው ጎልቶ ይታያል። ጩኸት ቁጣና ንዴት በሕይወቱ ዘመን ልማድ ይሆናሉ።

- ሰው አሳቡን ለሰይጣን ምሽግ እንዲሆን ከሰጠ የሚያስበው እንደ እግዚአብሔር ቃል ሳይሆን በራሱ አሳብ ይሆናል። የእግዚአብሔርን ቃል አያምንም። መንፈስ ቅዱስ የሚናገረውን ይንቃል ... ወዘተ።

- በአጋንንት ዓለም ተሳትፎ ከነበረ ደግሞ ያለበቂ ምክንያት መጫጫን፣ ቅዠት፣ እንቅልፍ ማጣት፣ የቃሉ ከልቡ መወሰድ፣ በጸሎት ማንቀላፋት፣ ማዛጋት፣ የአእምሮ መረበሽ፣ ወዘተ ይታይበታል። እነዚህ ነገሮች በቂ እረፍት ባለመውሰድ፣ ከሥራ ብዛት፣ በረሃብ ወዘተ ሊመጡም ስለሚችሉ ማስተዋል ተገቢ ነው።



## ምዕራፍ ሰባት

# አጋንንትን የምናወጣባቸው መሣሪያዎቻችን

አጋንንትን እንዴት እንደምናወጣ ከመመልከታችን በፊት አጋንንትን የምናወጣበት መሣሪያዎቻችንና ብርታታቸውን ማወቅ ተገቢ ይሆናል።

በዚህ ዓለም ላይ ሁለት ተቃራኒ ኃይላት አሉ። እነዚህም የእግዚአብሔር ኃይልና የሰይጣን ኃይል ናቸው። እኛ አማኞች የእሸናፊው የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን ደስ ይለናል። ሰይጣንና ሠራዊቱ የተሸነፉ ናቸው። ከሰይጣንና ከሠራዊቱ ጋር የምንዋጋው እንደ አዲስ ድል ለማድረግ ሳይሆን ድላችንን ለመጠበቅ ነው። እኛ የጌታ ወታደሮች ነን። ወታደር ደግሞ የመከላከያና የማጥቂያ መሣሪያ ይለብሳል፣ ይይዛል። የኛ ውጊያ መንፈሳዊ እንጂ ከደምና ከሥጋ ጋር ስላልሆነ መሣሪያዎቻችንም መንፈሳዊያን ናቸው። እጅግ ብርቱ የሆኑ ( 2 ቆሮ. 10:3-4) በዘመናችን እንዳሉ የጦር መሣሪያዎች መሻሻል የማይፈልጉ ሁልጊዜ ሕያውና ከሁሉም የላቁ ብርቱ መሣሪያዎች ተሰጥተውናል። መሣሪያዎቻችንም እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል:-

1. *የእግዚአብሔር ዕቃ ጦር*
2. *የኢየሱስ ስም*
3. *የእግዚአብሔር ቃል*
4. *የኢየሱስ ደም*
5. *የመንፈስ ቅዱስ ኃይል/የእግዚአብሔር ጣት*
6. *እጆችን መጫን*
7. *ምስጋናና አምልኮ*
8. *ጾምና ጸሎት*
9. *መናፍስትን የመለየት ስጦታ*

## 1. የእግዚአብሔር ዕቃ ጦር

> *"በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ። የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካሉ ከክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ። እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ*

*የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፡ የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ ... "* (ኤፌ. 6:10-18)

የእግዚአብሔር ቃል አንዳንድ ዕቃ ጦር አንሱ፣ ልበሱ አይለንም። "ሁሉንም ልበሱ" ይለናል። ይህ ልብሳችን ጌታ ኢየሱስ ራሱ ነው (ሮሜ 13:12-14) (ገላ. 3:27) የብርሃን ልብስ መልበስ ማለት ኢየሱስን መልበስ ነው። ጌታ ኢየሱስ እርሱ ራሱ ዕቃ ጦራችን ነው።

- የእውነት መታጠቂያ ኢየሱስ ነው።

*"እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።"*ዮሐ. 14:6

- የጽድቅ ጡሩር - ኢየሱስ ነው። *"የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ።"(1 ቆሮ. 1:30)*

- የሰላም ጫማ (ዮሐ. 14:27)
- እምነት (ጋሻ) (ዕብ. 12:2)
- የመዳን ራስ ቁር (ዕብ. 2:10)
- የእግዚአብሔር ቃል (ዮሐ. 1:1-14)

የእግዚአብሔር ዕቃ ጦር የምንለብሰው ጌታ ኢየሱስ ለእኛ ማንና ምን እንደሆነ በማመንና ያመነውንም በመናገር ነው። (Confession of Faitlr) ለምሳሌ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ ለኔ ሕይወት፣ ጽድቅ፣ መሠረት፣ ተስፋዬ፣ የጦር ዕቃዬ ነህ። የእምነቴ ምንጭ ነህ በቃልህ የተጠበቅሁ ስለሆነ አመሰግንሃለሁ። በዚህ ቀን በአንተ ውስጥ አለሁና ጠላቴ አያገኘኝም። በአንተ ብርቱ ነኝ። በአንተ የጠላቴን ምሽግ አፈርሳለሁ። በአንተ ከአሸናፊዎች ሁሉ እበልጣለሁ" እንለዋለን ሃሌሉያ!

## 2. የክርስቶስ ኢየሱስ ስም

በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ፍጥረት ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር የሚንበረከክለት ከስም ሁሉ በላይ ታላቅ ስም የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለው ስም ነው። ይህንንም ስም እግዚአብሔር አብ ያለ ልክ ከፍ ከፍ አድርጎታል።

- *ማንኛውንም ነገር የምናደርገው በጌታ በኢየሱስ ስም መሆን አለበት (ቆላ. 3:17)*



- *ሁልጊዜ ስለሁሉ አምላካችንና አባታችንን ስለሁሉ ማመስገን ያለብን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። (ኤፌ. 5:20)*
- *ከሰማይ በታች እንድንበት ዘንድ የተሰጠን ስም የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። (ሐዋ. 4:12)*
- *በመንፈስ ቅዱስ የታጠብነው የተቀደስነውና የጸደቅነው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። (1 ቆሮ. 6:11)*
- *ፈውስ የሚሠጠው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። (ሐዋ. 3:16)*
- *አጋንንትን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናወጣለን (ማር. 16:17፣ ሉቃ. 10:17፣ ሐዋ. 16:18፣ ኤፌ. 1:20-21፣ ፊሊጵ. 2:8-11)*

ጴጥሮስ እና ዮሐንስ መልካም በሚሏት በር ከመወለዱ ጀምሮ ሽባ የነበረውን ሰው በጌታ በክርስቶስ ኢየሱስ ስም ሲፈውሱት ሰዎች በራሳቸው ኃይልና ቅድስና ያደረጉት መስሏቸው ተገረሙ። ጴጥሮስ ግን ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ስም ክብር ሰጠ። (ሐዋ. 3:12-16)

ጌታ ኢየሱስ ስሙን የመጠቀም መብት ሰጥቶናል። በክርስቶስ ኢየሱስ ስም የምናገለግል ሁላችን በምድር ላይ የክርስቶስ ኢየሱስ አምባሳደሮች ነን። (2 ቆሮ. 5:20) ስለዚህም ጌታ ሲናገር በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ አለ። (ማር. 16:17) በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ስንመለከት ቤተክርስቲያን በኢየሱስ ስም አጋንንትን ታወጣ ነበር በሰይጣን አገልጋዮችም ላይ ፍርድ ታደርግ ነበር።

(ሐዋ. 5:3፣ 16፣ 8:7-9፣ 13:6-11፣ 16:16-18፣ 19:12-17፣ 24:36፣ 26:18)

*ጌታ ኢየሱስን በ1974 ዓ.ም. ከተቀበልኩኝ በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ ሳነብ በማር. 16:16 ያለውን በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ የሚለውንና በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ የሚለው ለምን በሕይወቴ አይታይም እያልኩ ራሴን እጠይቅ ነበር። በተለይ አንድ ጊዜ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ እያለሁኝ ከሳይንስ ፋካልቲ ቤተ መጻሕፍት ተናድጄ ስወጣ በቤተ መጻሕፍት በር አንድ ወንድም አገኘኝእርሱም:- ምን ሆንክ አለኝ?*
*እኔም:- "በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ" ይላል ታዲያ የት አለ የማወጣው አልኩት።*
*እርሱም:- መልሶ "በአጋንንት ለተያዘ ሰው ነጻ እንዲወጣ ጸልየህ ታውቃለህ?" አለኝ።*
*እኔም:- "አላውቅም" አልኩት*
*እርሱም:- "ታዲያ ይህንን ሳታደርግ ለምን ታዝናለህ ለምንስ ትናደዳለህ" አለኝ።*
*እኔም:- "እውነቱን ነው" ብዬ ጥናቴን ቀጠልኩኝ። ከአንድ ዓመት በኋላ ከዩኒቨርስቲ ግቢ በጠዋት ተነስቼ ለሰዎች እመሰክር ነበርና አንድ እሑድ ጠዋት ሂልተን ሆቴል ሲጨፍሩ ላደሩት ለመመስከር ከአራት ኪሎ በቤተ መንግሥት ግቢ ባለው ባዕታ ማርያም ቤተክርስቲያን አቋርጬ ለመሄድ ስል ወታደሮች "በር ተዘግቷል ማለፍ አትችልም" አሉኝ። እኔም ቀኑ እሑድ ነበርና በዚያ*

*ቤተክርስቲያን ብዙ ሰዎች ነበሩ። አንድ ሴት ጥቁር ልብስ ለብሰው ያለቅሳሉ ጠጋ ብዬ ስላሳዘኑኝ "እማማ ምን ሆነው ነው?" አልኳቸው*
*እሳቸውም:- "ልጆቼን ብሔራዊ ውትድርና ወሰዱብኝ ቤቴ ሊፈርስ ደርሷል ባለቤቴ ከቤት ስላባረረኝ ቀበሌ ነው ያደርኩት" አሉኝ። በጣም አሳዘኑኝ ለእኝህ ሴትዮ ከወንጌል በቀር ሌላ የሚያጽናናቸው የለም ብዬ ጌታን ሰበኩላቸው። በመጨረሻ እንጸልይ ስላቸው "አይሆንም" አሉኝ። እኔም ዛሬ ሂልተን ሳልሄድ ጊዜዬን ሁሉ እዚህ ልባክኜ አልሄድም እማማ እጸልይሎታለሁ ብዬ "ቤታቸውን የምትበጠብጥ አጋንንት በኢየሱስ ስም ውጣ" ስል ለካስ አጋንንት በሴትየዋ ውስጥ ኖሯል አጋንንቱ በጣም ጮኸ እኔም ለካስ ጌታ በእኔም ይሰራል ብዬ አንድ አልኩኝ። ሃሌሉያ!*

## 3. የእግዚአብሔር ቃል

የእግዚአብሔር ቃል ዓለማትን የፈጠረ ብርቱ ቃል ነው። ይህ ቃል ለዘለዓለም ጸንቶ የሚኖር ሲሆን ሕያውና ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ እጅግ የተሳለ ነው። በዚህም ርኩሳን መናፍስትን እናሳድድበታለን እናወጣበታለንም።

ጌታ ኢየሱስ በዲያብሎስ በተፈተነ ጊዜ ዲያብሎስን ያሸነፈው በእግዚአብሔር ቃል "ተጽፏል" በማለት ነው። ስለዚህ ለትክክለኛው ፈተና መመከቻና ማጥቂያ የሚሆን ተገቢ ቃል መስጠት ስላለብን በእግዚአብሔር ቃል መሞላት፣ ቃሉን መስማትና ማድረግም ይኖርብናል። *"የመንፈስ ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።" (ኤፌ. 6:18)* ጌታ ኢየሱስ በቃሉ አጋንንትን ያወጣ ድውዮችንም ይፈውስ ነበር። ከሁሉ በላይ ደግሞ ልደትን ይሰጣል።

> *"በመሸም ጊዜ አጋንንት ያደሩባቸውም ብዙዎችን ወደ እርሱ አመጡ በነቢዩ በኢሳያስ እርሱ ድካማችንን ተቀበለ ደዌያችንንም ተሸከመ የተባለው ይፈጸም ዘንድ መናፍስትን በቃሉ አወጣ የታመሙትንም ሁሉ ፈወሰ።" (ማቴ. 8:16-17፤ ኤፌ. 6:18)*

## 4. የኢየሱስ ደም

የኢየሱስ ደም ስለ ኃጢአታችን የፈሰሰ፣ እግዚአብሔር አብን ያረካ፣ ሰይጣንን ድል የነሳ፣ እኛን የዋጀን፣ ሕይወት ከሌላቸው ከብርና ከወርቅ የሚበልጥ ክቡርና ሕያው የሆነ ደም ነው። የኢየሱስ ደም እኛን ከዲያብሎስ ቀንበርና ከግዛቱ ነጻ ያወጣን ብርቱ መሣሪያ ስለሆነ ሰይጣን እጅግ ይፈራዋል። *ራዕ.* 12:10-11



በተለይ በአጋንንት ለታሰሩት ስለ ደሙ መመስከር አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ደሙን በእምነት ሲቀበሉ ለእስራታቸው ምክንያት የሆነው የኃጢአት ሰንሰለት ይበጠሳልና ነው።

ሁላችንም ሰይጣንን በበጉ ደምና በምስክራችን ቃል ድል እንነሳዋለን። በተለይም የምስክራችን ቃል ስለ ድል አድራጊው የበጉ ደም መሆን አለበት። ምስክርነታችንም:-

- *በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ነጽቻለሁ (1 ዮሐ. 1:7)*
- *በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ወደ አብ መቅረብ አለኝ (ኤፌ. 2:12-13)*
- *በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ጸድቄአለሁ (ሮሜ 5:8-9)*
- *በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ተቀድሻለሁ (ዕብ. 13:12)*
- *በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለኝ (ቆላ. 1:20)*
- *በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ተገዝቻለሁ (ሐዋ. 20:28)*
- *በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ኅሊናዬ ነጽቷል (ዕብ. 9:14)*
- *የክርስቶስ ኢየሱስ ደም ለእኔ ክቡር ነው (1 ጴጥ. 1:19)*
- *የክርስቶስ ኢየሱስ ደም ክጠላት የምንሸፈንበት ነው። (ዘጸ. 12)*

## 5. የመንፈስ ቅዱስ ኃይል

በመንፈሳዊ ውጊያ የሚያበረታን የኢየሱስን ሕያውነት በሕይወታችን እውን የሚያደርግልን ጌታ መንፈስ ቅዱስ ነው።

ጌታ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሳይቀባ ለአገልግሎት አልወጣም ነበር። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የዲያብሎስን ስራ አፈረሰ፣ መልካም አደረገ፣ ለዲያብሎስ የተገዙትን ነጻ አወጣ።

> *"እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፤ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበርና።" (ሐዋ. 10:38)* *ሉቃ.* 3:21-23

እኛም ወንጌልን ለመስበክ መንፈስ ቅዱስ መሞላት እንዳለብን ጌታ ኢየሱስ ነግሮናል። ሐዋ. 1:8 በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አጋንንትን ማውጣት የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችን የመሆንዋ ትልቅ ምልክት ነው። ሉቃ. 11:20 መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ጣት ተብሎ ተጠርቷል። ይህ ጣት አጋንንትን ያወጣል፣ በእግዚአብሔር ላይ የሚነሱትንም ያንበረክካል፣ ቀንበርንም ይሰብራል።

# ምዕራፍ ስምንት
# አጋንንትን ማውጣት

አጋንንትን ከሰዎች ውስጥ ማውጣትና ያሰራቸውን ሰንሰለት መበጣጠስ እግዚአብሔር በጣቱ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚያደርገውና የእግዚአብሔር መንግሥት በሰዎች መካከል የመገለጽዋ ምልክት ነው ማቴ. 12 ይህም ክርስቶስ ኢየሱስ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር እንደተሰጠው ያሳየናል።

## 8.1 አጋንንት ካደሩበት ሰው ውስጥ አጋንንትን ማውጣት

አጋንንትን ለማውጣት በመጀመሪያ ልብ ማለት ያለብን ሰውዬው አእምሮውን ካልሳተ በስተቀር የሰውዬውን ፈቃድ ማግኘት ወሳኝ እንደሆነ ነው። ሰውዬው በንስሐ ወደ እግዚአብሔር መመለስና ሰይጣንን መካድ ይጠበቅበታል።

አጋንንትን ስናወጣ ልናደርጋቸው የሚገቡ ነገሮች:-

### ሀ. አጋንንትን ማሰር ማቴ. 16:19

ይህም ክፉ ሥራቸውን እንዳይሠሩና ሰውዬውን ወይም ሌሎች ሰዎችን እንዳይጎዱ ማዘዝ ነው። ብዙ እንዳይናገሩም መከላከል ይሆናል።

ማር. 3:27 ሉቃ. 4:35

### ለ. የአጋንንቱ አለቃ እንዲወጣ ማዘዝ ሉቃ. 4:35

አንድ የአጋንንት አለቃ በሰሩ ጭፍሮች አሉት እንዲወጣ የምናዘው አለቃውን ነው። አለቃው ሲወጣ ሁሉም ከእርሱ ጋር አብረው ይወጣሉና። ይህም "የ ... መንፈስ በጌታ በኢየሱስ ስም አዝሃለሁ ውጣ!" ማለት ነው።

በማር. 1:23-26 ብንመለከት ተናጋሪው መንፈስ አንድ ነው። ይህ አለቃው ነው። ሲናገር ግን ሌሎቹን ሁሉ ወክሎ ነው። ጌታም ሲገሥጸው ውጣ! ብሎ ነው ሰዎቹ ሲናገሩ ግን ... በሥልጣን ርኩሳን መናፍስትን ያዛል እነርሱም ይታዘዙለታል ... አሉ።

በማር. 5:1-13 ያለው ርኩስ መንፈስ ከሥሩ ሌጌዎን ነበሩ ማለትም ከ3000 - 6000 አጋንንት ማለት ነው። ጌታ ውጣ ብሎ የገሰጸው አለቃውን ነው።



አለቃው ሲወጣ ጀሌው ይከተላል።ነገር ግን በአንድ ሰው ከአንድ አለቃ መንፈስ በላይ ከገባ ሁሉንም አለቆች በየተራ ማውጣት ይገባል።

ለምሳሌ:- እንበል በአንዲት ሴት ውስጥ የቡዳ መንፈስና የዛር መንፈስ ቢኖርባት የቡዳው መንፈስ አስር ቢሆኑና የዛር መንፈስ ደግሞ ሰላሳ ሁለት ቢሆኑ የቡዳውና የዛር መንፈስ አስከነ ጭፍሮቻቸው ማውጣት ተገቢ ነው። ያለበለዚያ የቡዳው መንፈስ ብቻ ወጥቶ የዛር መንፈስ ቢቀር ሴትዬዋ ነጻ አይደለችም አንዱ መንፈስ ቀርቷልና። ሴትየዋ ነጻ የምትሆነው ሁለቱ መናፍስት ሲወጡ ብቻ ነው።

### ሐ. አጋንንቱ ከወጡ በኋላ ተመልሰው እንዳይገቡ ማዘዝ

*"ኢየሱስም ሕዝቡ እንደገና ሲራወጥ አይቶ ርኩሱን መንፈስ ገሰጸና አንተ ዲዳ ደንቆሮም መንፈስ እኔ አዝሃለሁ ከእርሱ ውጣ እንግዲህም አትግባበት አለው።" (ማር. 9:25)*

የወጡ አጋንንት ሰውዬው እንደሚገባ ለወንጌል ካልኖረ፣ በሕይወቱ በቃሉ እውነት ካልተያዘ መልሰው ለዛውም ተደራጅተው ይገቡበታል። ለዚያ ሰው ከፊት ይልቅ ይብሰበታልና ሰዎች አጋንንት ከወጡላቸው በኋላ ልናደርግላቸው የሚገባንን ነገር በሚቀጥሉት ገጾች እንመለከታለን።

### መ. አንዳንድ ጊዜ አጋንንት ሳለመውጣት ይታገላሉ ይተጋገዛሉም።

*"ርኩሱንም መንፈስ ከሰውዬው እንዲወጣ <u>ያዘው ነበርና።</u> ብዙ ዘመንም ይዞት ነበርና በሰንሰለትና በእግር ብረትም ታስሮ ይጠበቅ ነበር እስራቱንም ሰብሮ በጋኔኑ ወደ ምድረ ባዳ ይነዳ ነበር። "*
*(ሉቃ. 8:29)*

በዚህ ቦታ ላይ ስንመለከት አጋንንቱ እንደተገዳደረና ከመቅጽበት እንዳልወጣ ያሳያል በሉቃ. 11:14 *"ዲዳውንም ጋኔን <u>ያወጣ ነበር</u> ጋኔኑም ከወጣ በኋላ ዲዳው ተናገረ።"* ስለሚል ጋኔኑ የወጣው ከመቅጽበት ሳይሆን ጊዜ እንደወሰደ ያመለክታል። አጋንንት ሲገዳደሩ በመጽናት መገሰጽና የኅብረት ጸሎት አስፈላጊ ነው።

*አጋንንት በሽታ እንደሚያመጡ ቀደም ሲል ተመልክተናል። እንዲህ ሲሆን አጋንንቱ የያዘው በሽታና መርገም ሁሉ ይዞ እንዲወጣ ማዘዝ ተገቢ ነው። አጋንንቱ ሲወጣ በሽታውም አብሮ ይጠፋል።*

*በየካቲት 19/1997 እ.ኤ.አ. በምዕራብ አውስትራሊያ ግዛት በፐርዝ ከተማ International Christian Fellowship በተባለ የነጮች ቤተክርስቲያን*

- ቀደም ሲል በመናፍስት ዓለም የነበረው ግንኙነት
- የሚያነባቸው መጻሕፍት ራምፓ፣ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ፣ ፖርኖግራፊ ማለትም የርኩሰት መጻሕፍት
- የሚውልበት ቦታና ሰዎች፣ በአጋንንት ከተያዘች ሴት ጋር የተደረገ ግብረ ሥጋ ግንኙነት
- ከተለያዩ  ሱሶች መላቀቁን ማረጋገጥ
- የጋብቻው ሕይወት፡- ያላገባ - ያገባ - የፈታ
- ውርጃ ካደረገች
- ከወላጆች ጋር ያለ ግንኙነት
- የሥራው ፀባይ
- የሚማርበት ትምህርት ቤት

የእስራት ምንጭ ለመለየት መናፍስትን የመለየት ስጦታ ወደር የሌለው ነው።

በተለይም የእስራቱ ምንጭ ከመናፍስት ዓለም (Occult Involvement) ከሆነ ከፍተኛ ጭንቀት፣ ፍርሃት፣ በጆሮ ውስጥ ሌላ ድምጽ መስማት፣ በመንፈሳዊ ሕይወት ደግሞ መንፈሳዊ ዕውርነትና ዲዳነት፣ ድንቁርና፣ መንፈስ ቅዱስ ሙላትን እንዳይቀበሉ መከልከል፣ ጸሎት ሲጸልይ እርግጠኛ አለመሆን ወዘተ ስለሚያመጣና ከወላጆችና ከቤተሰብ የሚተላለፍ በመሆኑ ከመጸለያችን በፊት ለሰዎቹ በደምብ ምክር መስጠት ያስፈልጋል። ይህም ጌታ ኢየሱስ ብቻ ከዚህ እስራት ነጻ እንደሚያወጣቸው መመስከር ነው። ገብተውበት የነበረው የአጋንንት ዓለም የኃጢአት ዓለም መሆኑን አውቀው እንዲናዘዙ ማድረግ (ዘሌዋ. 19:26፣ 31:20፣ 6:27፣ ዘዳ. 18:10-12)

ሰውዬው ድምጹን ከፍ አድርጎ አጋንንቱን በክርስቶስ ኢየሱስ ስም እንዲክድ ማድረግ ከቤተሰብ ይሁን ከጠንቋይ ቤትና ከመሳሰሉት የተቀበላቸውን የተለያዩ ድግምት ያለባቸውን ነገሮች ማቃጠል።

## 3. በጌታ ኢየሱስ ስምና በመንፈስ ቅዱስ ቅባት ሰንሰለቱን መስበር

*ይህ እጆችን በመጫን ወይንም የእግዚአብሔር ቃል በመናገር የአጋንንትን ሰንሰለት መስበር ነው።*

> *"ስለዚህ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በጽዮን የምትኖር ሕዝቤ ሆይ፣ አሶር በበትር ቢመታህ፣ ግብፅም እንዳደረገ ዘንጉን ቢያነሳብህ አትፍራው። ቁጣዬ እስኪፈፀም መዓቴም እስኪያጠፋቸው ድረስ ጥቂት ጊዜ ቀርቶአልና። የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም ምድያምን በሔሬብ አለት በኩል እንደመታው ጅራፍ ያነሳበታል በበትሩም በባህር ላይ ይሆናል፣ በግብፅም እንዳደረገ ያነሳዋል። በዚያ ቀን ሸክሙ ከጫንቃህ ቀንበሩም ከአንገትህ ላይ ይወርዳል ቀንበሩም ከውፍረት የተነሳ ይሰበራል።" (ኢሳ.10:24-27)*



# ምዕራፍ ዘጠኝ
# ምክር ለአገልጋዮች

አጋንንትን በማውጣት የሚያገለግል ሰው ሌላውን ከተያዘበት የአጋንንት ኃይል ነጻ ለማውጣት፣  አጋንንትን ለማባረርና ለማሰር ስለሆነ ግብግብ የ[illegible]ፀት መንፈሳዊ ውጊያ እያካሄደ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልገዋል። ስለዚህም በዚህ አገልግሎት የሚያገለግል አንድ አገልጋይ ማድረግ ያለበት ከሞላ ጎደል እንደሚከተሉትን ነው።

**1. ትሁት መሆንና እግዚአብሔርን መታዘዝ ያዕ. 4:7**

ትዕቢትና በራስ መመካት ከጌታ የተቀበልነውን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚያርቁና አደገኛ ኃጢአቶች ስለሆኑ ዘወትር መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ጌታ ኢየሱስ ትሁትና ታዛዥ ስለነበረ አጋንንት በፊቱ ሊቆሙ አልቻሉም። (ማቴ. 11:29)

ትህትና ማለት መሽኮርመም ሳይሆን እግዚአብሔር የሠራውን እግዚአብሔር ነው ያደረገው ብሎ በፍፁም ልብና በአንደበት መመስከር ነው።

**2. የቅድስና ሕይወት መኖር**

አጋንንት ርኩሳን ስለሆኑ ቅድስና እንደ እሳት ይፈጃቸዋል። ሕይወታችን ካልተቀደሰ አጋንንት ምንም አይነኩም።

**3. ክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀልና በትንሳኤ ላይ የሠራውን ሥራ ማወጅ**

**4. አጋንንትን ለማውጣት እምነት አስፈላጊ ስለሆነ እምነት ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ ቃሉን መብላትና ማድረግ**

**5. አጋንንት ለማውጣት**

- ቢቻል ሌሎች በጸሎት የሚያግዙህ ክርስቲያኖችን ከአንተ ጋር አቁም
- ለተቃራኒ ጾታ ብቻህን ወይም ብቻሽን አትጸልይ/ዪ
- ንገትህ ላይ እንደ ክራቫት አይነት ነገር ካለ ማውለቅ መልካም ይሆናል ምክንያቱም ሲወራጩ ክራቫትህን ቢስቡብህ እንዳትታነቅ ነው።
- ለሴቶች በሚጸለይበት ጊዜ ብዙ ሲወራጩ ሰውነታቸው እንዳይገላለጥ ጋቢ ወይም ነጠላ ነገር ከወገባቸው በታች ማልበስ ተገቢ ነው። አጋንንት የሰውን አሳብ ለመስረቅ ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ነውና።
- ንት ብዙ እንዲለፈልፉና ሚስጢር ተናገር በማለት ከአጋንንት መረጃን አለመቀበል። ጋኔኑ የተያዘውን ሰው እገድለዋለሁ አትገስጸኝ ቢል የተለያዩ

# ምዕራፍ አስር

# አጋንንት የወጡለት ሰው የሚያገኘው በረከት

እግዚአብሔር መልካም ነው መልካም ነገርን ይሰጣል። አጋንንት ከሰው ሕይወት ለቀው ሲወጡ ለሰውዬው፣ ለቤተሰቡና ለህብረተሰቡ ትልቅ በረከት ነው። በረከቶቹም:-

## 1. በሰውዬው ውስጥ ሆነው ሲያስጨንቁት የነበሩ አጋንንት ከመውጣታቸው የተነሣ ነጻ ይሆናል።

ይህም የልብ እረፍትና የአእምሮ ሰላም ማግኘት ነው። ከፍርሃት፣ ከቅዠት፣ ከተለያየ ድምጽና በአእምሮ ከሚሳሉ ምስሎች፣ ከሞት ፍርሃት፣ ነፍስና ሥጋው ነጻ ይሆናል።

## 2. ሰውዬው በሽተኛ ከነበረ ጋኔኑ ሲወጣ በሽታውም አብሮ መወገዱ በረከት ነው።

*"እነርሱም ሲወጡ እነሆ፣ ጋኔን ያደረበት ዲዳ ሰው ወደ እርሱ አመጡ። ጋኔኑንም ካወጣው በኋላ ዲዳው ተናገረ።" (ማቴ. 9:32-33* ፣12:12-22፣ ሉቃ. 13:10-13፣ 9:38-42*)*

## 3. ሰውዬው በአጋንንት ኃይል ሲሠራና ሲያደርግ የነበረው የክፋት ሥራ ይቆማል (ሐዋ. 16:16-18)

የሚጠነቁል የነበረ ጋኔኑ ሲወጣ የመጠንቆል ኃይሉ ይጠፋል። ምትሃት ሲያደርግ የነበረ የምትሃት መንፈስ ሲወጣ ሰውዬው ያንን ሊያደርግ አይችልም። በአጠቃላይ በአጋንንት የሆነ ማጭበርበርና ማታለል ይጠፋል።

## 4. የማህበራዊና የሥነልቦና ፈውስ

*"... አጋንንትም የወጡለትን ሰው ለብሶ ልቡም ተመልሶ በኢየሱስ እግር አጠገብ ተቀምጦ አገኙትና ፈሩ።" (ሉቃ. 8:35)*



ይህ ሰው በአጋንንት ኃይል ሰው አላሳልፍ ያለ፣ ሰውነቱን የጎዳ፣ ማህበራዊ ነገሩ ሁሉ የተበላሸበት ነበር። ጌታ ኢየሱስ ነጻ ካወጣው በኋላ አራት ትላልቅ ነገሮች ሆኑለት እነዚህም:- ልቡ ተመልሶ አእምሮው ጤናማ ሆነ፣ ልብስ ለብሶ እርፎ መቀመጥ ቻለ፣ ወደ ቀዬውና ቤተሰቦቹም ተመልሶ ወንጌላዊ ሆነ።

*በ1984 ዓ.ም በድሬዳዋ ከተማ ከድር የሚባል አእምሮውን የሳተ ሰው ያገኘውን የሚበላ፣ ራቁቱን የሚሄድ፣ ፀጉሩ ቆጥርጥር ያለ፣ ሙሉ ሰውነቱ በግራሶና በአፈር የተበላሸ ነበር። ክርስቲያኖች ወደ ጸሎት ሥፍራ ይዘውት መጡ። ከተያዘበት የአጋንንት ኃይል ነጻ እንዲሆን በክርስቶስ ኢየሱስ ስም ስገስጽ 77 አጋንንት ወጡለት። ከወጡለት በኋላ በደስታ ብዛት ሰገደ ወገኖች ልብስ አመጡለትና ለብሶ እሀቶችም ጸጉሩን ላጩት እግሩን ሲታጠብ "ምን ሆኜ ነበር? ይሄ ሁሉ ጭቃና ግራሶ ብቻ እስኪሆን ድረስ" አለ። የኢየሱስ ስም ፍፁም ጤና ስለሰጠው ትተውት የነበሩ ቤተሰቦቹ መጥተው ወሰዱት።*

## 5. የሕይወት አቅጣጫ የመለወጥ በረከት

በሉቃ. 13:13 ሰይጣን ያሰራት ሴት ጌታ ኢየሱስ ከእስራትዋ በፈታት ጊዜ እግዚአብሔርን ማክበር ጀመረች። በማር. 5:18 በሌጌዎን መንፈስ አእምሮውን ስቶ የነበረው ሰው አጋንንት ከወጡለት በኋላ ኢየሱስን ለመከተል ለመነ። ጌታ ግን የእግዚአብሔርን መልካምነት ሂድና ተናገር አለው። ማር. 5:19 እርሱም በዲቃፖሊስ ሄዶ ወንጌል ሰበከ ይላል። ጌታ ኢየሱስ እየዞረ በሚያገለግልበት ጊዜ በገንዘባቸው ይረዱት ከነበሩት ሴቶች መካከል ሰባት አጋንንት የወጡላት መግዳላዊት ማርያም ነበረች። (ሉቃ. 8:1-3)

በአጠቃላይ ጌታ ከአጋንንት ነጻ ያወጣቸው የጌታን ታላቅ ውለታ በማሰብ ጌታን እጅግ ይወዱታል። የቀድሞው ሕይወታቸው አስጨናቂ ስለነበር ወደዚያ መመለስም አይፈልጉም።

# ምዕራፍ አስራ ሁለት

# በነፃነት መኖር

*"በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ።" (ገላ. 5:1፣ ዮሐ. 8:31-32)*

በክርስቶስ ኢየሱስ ነጻ የወጣ ሰው

## 1. ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትን ያደርጋል (ማቴ. 4:4 ዕብ. 4:12)

ይህም በቃሉና በጸሎት ነው።

*"የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።" (2 ጢሞ. 3:16-17)*

## 2. ኃጢአቱን ይናዘዛል

*"ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመጻም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።" (1 ዮሐ. 1:9)*

## 3. እግዚአብሔርን ይታዘዛል ያገለግላል (ሐዋ. 5:29)

*"... የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን። የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም የምትሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም።" (ዮሐ. 14:23-24)*

## 4. እግዚአብሔርንና ሰዎችን ይወዳል (ማቴ.22:34-40)

*"ነገር ግን ለምትሰሙ እላችኋለሁ ጠላቶቻችሁን ውደዱ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ የሚረግሙአችሁንም መርቁ ስለሚበድሉአችሁም ጸልዩ።" (ሉቃ. 6:27-28)*

## 5. ስለማናቸውም ነገር በእግዚአብሔር ይታመናል

*"በፍፁም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን በራስህም ማስተዋል አትደገፍ።" (ምሳሌ 3:5-6)*

## 6. ይቅር ይላል በሌሎችም አይፈርድም

*"አትፍረዱ አይፈረድባችሁምም አትኰንኑ አትኰነኑም። ይቅር በሉ ይቅር ትባላላችሁ። ስጡ ይሰጣችሁማል በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና። የተጨቆነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም*



*መልካም መስፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል።" (ሉቃ. 6:37-38)* (1ቆሮ. 11:30-31)

## 7. የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ይሰጣል

*"ይህንም እላለሁ በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል። እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ በኃዘን ወይም በግድ አይደለም" (2 ቆሮ. 9:6-7)*

## 8. ከክርስቲያኖች ጋር ኅብረትን ያደርጋል

*"... በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።" (ሐዋ. 2:42)*

## 9. በጌታ ደስ ይሰኛል

*"ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ ፤ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ።"*
(ፊሊ. 4:4)
*"ነገሩ ግን ሲገለጥ ደግሞ ሐሴት እያደረጋችሁ ደስ እንዲላችሁ በክርስቶስ መከራ በምትካፈሉበት ልክ ደስ ይበላችሁ።"*
*(1 ጴጥ. 4:13)*

## 10. ለሌሎች ጌታን ይመስክራል ሐዋ. 1:8

*"ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ።" (ማቴ. 10:32-33)*

## 11. በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወት አለው

*"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ።" (ሐዋ. 1:8)*

## 12. ከጌታ ጋራ አንድ እንደሆነና ኅብረት እንዳለው ለመግለጽ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም በውኃ ይጠመቃል፣ የጌታን ራት ይካፈላል።

"እናንተ ግን፣ ወዳጆች ሆይ፣ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ ወደ ዘለዓለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምህረት ስትጠባበቁ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ። አንዳንዶች ተከራካሪዎችንም ውቀሱ፣ አንዳንዶችንም ከእሣት ነጥቃችሁ አድኑ፣ አንዳንዶችንም በሥጋ የረከሰውን ልብስ እንኳ እየጠላችሁ በፍርሃት ማሩ።

ሳትሰናከሉም እንዲጠብቃችሁ በክብሩም ፊት በደስታ ነውር የሌላችሁ አድርጎ እንዲያቆማችሁ ለሚቻለው ብቻውን ለሆነ አምላክና መድኃኒታችን ከዘመን ሁሉ በፊት አሁንም እስከ ዘለዓለምም ድረስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ግርማ ኃይልም ሥልጣንም ይሁን አሜን።"

(ይሁዳ 20-25)